

ሳህሌ ገ/ማርያም መሸሻ
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ጥቅምት **1970** (የቀይ ሽብር ሰለባ)

# ኢትዮጵያ

ሰኔ | **1**ኛ ዓመት ልዩ እትም | በነፃ የሚሠራጭ

*ርእሰ አንቀጽ* ገፅ 2
ዘር ማጽዳት ፡-ኢትዮጵያዊነትን አሰልስሎ መግደያ የወያኔ ሤራ፤

*ዜና ከተባለ* ገፅ **3**
ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት ለአባይ ግድባችን ታረጂልን አሏት ።

*ምን ይሰማ... ኣገር* ገፅ **3**



*ትላንትና* ገፅ **5**
*የቦረና ነጋሌዎቹ የኢሕአፓ ወጣቶች ሕዝባዊ ገድል በጨረፍታ ቅኝት*

**ነፃ ሀሳብ** ገፅ **6**
ቃታር/ካታር- - -አደገኛ ትንሽ ሀገር

## ልዩ እትም

### ጋዜጣችን


ወርሀዊው ኢትዮጵያ ጋዜጣ ለንባብ መቅረብ የጀመረበትን አንደኛ አመት ለማክበር እየተዘጋጀ ነዉ። የማንነታችን ምልክት፤ የነጻነታችንም ዓርማ፡ የብሔራዊ ልእልናችን መታወቂያ የሆነችውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከጋዜጣው የመጀመርያ ገጽ ላይ ማድረጋችን ያለምክኒያት አይደለም። የብሔራዊ ነፃነት ዓርማችን በመሆኗ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለእኛ ለጋዜጣዋ አዘጋጆች ልዩ ትርጉምና ኩራት ስለሚሰማን ነው። የነጻነት ዓርማ፤ የብሔራዊ ኩራታችን ማሳወቂያ፤ የማነነታችን መግለጫ የሆነችውና በአያት ቅድመ-አያቶቻችን የተቀደሰ ደም ዋጋ የተከፈለበት ሰንደቅ ዓላምችን፤ ዛሬ በአገር በቀል ጠላቶች አፍ "ብጣሽ ጨርቅ" ተብላ ስትዋረድ፤ እኛ ልጆቿ ከወደቀችበት ትብያ አንስተን ሰንደቋን ከፍ አድርጎ ማውለብለብ የዜግነት ግዴታችን መሆኑን ስለምናምንበት በኢትዮጵያ ጋዜጣ የፊት ገጽ ላይ ብሐራዊ ሰንደቅ ዓላማችንን ማሰቀመጠጥ ታሪካዊ ግዴታችንን እንደተወጣን እንቆጥረዋለን። ይህንንም በማድረጋችን፤ ከመላው አንባቢያን ያልተቋረጠ -ያልተቆጠበ ድጋፍንና ትብብር፤ ይመጣልናል ይህም ለሰራችን ትጋትን፤ ብርታትንና ንቃትን ሰጥቶናል።

ይህ በዋሽንግተንና አካባቢ የኢሕአፓ ድጋፍ ኮሚቴ አካል ተቋቁሞ የሚታተመው ኢትዮጵያ ጋዜጣ ዓላማውና ተግባሩ፤ ጥራት ባለውና በመረጃ የተደገፈ የዜና አቅርቦት ለአካባቢያችን ህብረተሰብ መስጠት ነው ወያኔና ቅጥረኞቹ የዲያስፖራውን ህብረተስብ ለማወናበድ የሚነዙትን ፕሮፖጋንዳ በቅርብ እየተከታተልን ለማጋለጥ ገንቢ የሆነ፤ ዕዉነተኛና ትክክለኛ ዜና ሀተታና ዘገባ እናቀርባለን። ለኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ትክክልኛውን ዜና በማቅረባችንም ከአንባቢዎቻችን የተባና የነቃ ትብብር አልጎደልብንም ። ድጋፋችን ለኢሕፓ ወገንተኛንታችን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ስለሆነ፤ በፃነ ተመስርተን፤ ለነፃነት ቆመን ነፃ ጋዜጣ እያተምን ለወገናችን ለኢትዮጵያ ህዘብ ነፃ ኢንፎርሜሽን እናበርከታለን። ይህ ለኢትዮጵያ ህዝብ ልናገለግለው ከሚገባን ንዑስ ክፍል ነው። ሀገራችንን ከዘረኞች ቀንበር ነፃ ለማውጣት በሚደረግው ብሔራዊ የነፃነት ትግል ውስጥ ትክክለኛ ዜና አቅርቦትና ስርጭት የሚጫወተው ሚና ወሳኝ መሆኑን ስለምንገነዘብ፤ በዚህ ረገድ ሊከናወን የሚችለዉን ዉሉ ሳንታክት እንፈሥማለን። የሕብረተሰቡ ሙሉ ደጋፍና ትብብርም እስካሁን አልተለየንም። ወደፊትም የጋዜጣችን አገልግሎትና ስርጭት እየሰፋና እያደገ በሄደ ቁጥር የኀብረተሰባችን የሞራል፣ የቁሳቁስና፣ የነዋይ ድጋፍና ርዳታ እየጨመረ እንደሚሄድ አንጠራጠርም። ከአንባቢዎቻችን የሚላኩልንን ጽሁፎች ሁሉ እናስተናግዳለን። አንድ ነፃ ጋዜጣ ነፃ መሆኑ የሚረጋገጠው፣ የሁሉም ዜጋ ያልተገደበና ያልተከደከደ ሙሉ ተሳተፎና ትብብር ሲያገኝ በመሆኑም ፤ ማንኛውም አንባቢ ኀሳቡን በነፃ የሚገልፅበት ነፃ ጋዜጣ ስለሆነ ሁሉም እንዲሳተፍ እንጋብዛለን።

በአሁኑ ጊዜ ሃገራችን በዘረኞች አምባገነን ሥርዓት ጭቆና ሥር በመዉደቋ ምክንያት ነፃ ጋዜጦች ደብዛቸው ጠፍቷል። ጋዜጠኞች ፀሀፊዎች ፤ድራሲያን፤ የሕሊና ሰዎች ሁሉ ወኅኒ ወርደዋል። የዴሞክራሲ ጭላንጭል እንኳ ሰለማይታይ፤ መላው ሕዝብ ሙብቱ ታፍኗል። ከወያኔ አሰልቺና አንገፍጋፊ የፕሮፐጋንዳ ልፈፋ በስተቀር፣ የተለየ ዜና ማግኘት አልቻለም። አማራች ዜና የማግኘት እድሉ ተዘገግቶበታል። የኤሊክትሮኒክስ አገልግሎት ሁሉ ስለታፈነበት፣ የኢንተርኔት ተጠቃሚ አልሆነም። የውጭ ሬዲዮ ጣቢያዎችና የቴሌቭዥን አገልግሎቶች ወደ ሀገሪቱ መግባት ስለተከለከሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከመላው ዓለም ተገሎ በጨለማ ውስጥ ይኖራል። እንደጨለማው ክፍለ ዘመን ይህንን ሁኔታ ለማስወገድ፤፤ በኢትዮጵያ በግድ መሰረታዊ ለውጥ መምጣቱ የሚያከራክር አይሆንም። ተወደደም ተጠላ፣ ይዋልም ይደር ለውጥ መምጣቱ ግን ማንም ዜጋ አይጠራጠርም። በሀገራችን ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ሁሉ ኢትዮጵያ ጋዜጣ የድርሻዋን ማበርከቷን ትቀጥላለች። ጋዜጣዋ ዕትመት የጀመረችበት አንደኛ አመት ስታከብር፣ ሁላችሁም የዘውትር ድጋፋችሁን እንድምትቀጥሉ የጋለ ዕምነታችን ነው።

## ኢትዮጵያ ጋዜጣን

*በተለያዩ ድ`ረ ገጾች
ሀ. **Eprp.com**
ለ. **Asimba.org**
ሐ. **Debteraw.com**
ወዘተ.
*በ **Face book (ethiopianewspaper)**






# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢው ደጋፊ አካል**

**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011
ስ/ቁ 202 291 4217
ኢሜል dc.region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

### ዘር ማጽዳት ፡-ኢትዮጵያዊነትን አሰልስሎ መግደያ የወያኔ ሤራ፤

ሰሞኑን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ተሰራጭተዉ የሚኖሩ ሕዝባቸዉን ወዳድ ኢትዮጵያዉያን በወያኔ ላይ ቁጣቸዉን ሲያስደምጡ ሰንብተዋል ። መነሻዉ የተለመደዉ የወያኔ፤ ዜጎችን ዘር ቆጥሮ የመንቀልና ከኑሮ የማፈናቀል እኩይ ተግባር ነዉ ። ዘርና ቋንቋን መስፈርት አድርጎ መስተዳድሩን የዘረጋዉ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዉያን በአገራቸዉ ምድር ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ተዘዋዉረዉ ለመሥራትና በመረጡት ቀዬም ለመኖር ያላቸዉን የማይገሰስ መብት ይጻረራል ። በስዉርም ሆነ በግልጽ ይዋጋዋል። ወያኔ የተሠራበት ማግ - ጠባብ ጎሰኝነት ፤ ድሩ ደግሞ የለየለት ጸረ- ኢትዮጵያዊነት ነዉ ። በሕዝብ ጫንቃ ላይ በጉልበት የጫነዉ አምባገነናዊ ሥርዓቱ ማዝመሙን በተረዳ ቁጥር ደግሞ ያጠለቀዉ የ "ዴሞክራትነት" ጭምብል ሳይቀር ይወልቅበታል ። በደመ ነፍስም ወደ ተፈጥሯዊ ባህሪዉ ተመልሶ በመሠሪ ተግባሩ ይገፋበታል ። ከሰሜን እስከደቡብ ፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በተዘረጋዉ የሀገሩ ምድር ላይ የሠፈረዉን ዜጋ ያዋክባል ፤ ያሳድዳል ፤ ያስራል ፤ ይገድላል ። ለግፉ ዳርቻ ፤ ለሰቆቃው ወሰን የለዉም። ልዩነት ቢኖር የተራ ጉዳይ ብቻ ነዉ ። በአገዛዙ የሃያ ሁለት ዓመታት ዕድሜ ዉስጥ ያስተዋልነዉ ነዉና ፤ ከአርባ ጉጉ የሚጀምረዉ የግፉዐን ዜጎች ሞትና ከኑሮ መፈናቀል ዛሬ ቤንሻንጉል ላይ ደርሶ ያቆማል ብሎ ማሰብም ከምኞት አያልፍም ።

የዚያኑ ያህልም ፤ "ፌዴሬሽን" በሚል ስያሜ ባዋቀረዉ የጎሣዎች ክልላዊ ስብስብ ዉስጥ በሚገኝ በየትኛዉም ኬላና ጉጥ የሚወሰዱ ርምጃዎች ሁሉ የወያኔን ዘረኛ ፖሊሲዎች ተከትለዉ የሚፈጸሙ መሆናቸዉ ሊሰመርበት ይገባል ። ለነዚህም ተጠያቂዉ ወያኔ እንጂ ሌላ ዋቢ የሚያልፍ ወገን ሊመጣ አይችልም።ሌላዉ በአንክሮ ሊጤን የሚገባዉ ጉዳይ ወያኔ ወር-ተራ አስይዞ በሕዝብ ላይ የሚያደርሰዉ በደል፤ በተቃዉሞ የሚነሳበትን ወገን የመከፋፈል ተደራቢ ሤራ አዝሎ የሚፈጸም መሆኑ ነዉ ።ዛሬ ፤ ጋምቤላ ዉስጥ ለሚፈጸም ወንጀል አምርረዉ የሚጮሁት ከአኙዋክ የሚወለዱ ኢትዮጵያዉያን ብቻ ከሆኑ ፤ ነገ አፋር ዉስጥ ለሚደረግ ወያኔያዊ ግፍ የተቃዉሞ ምላሽ ሰጪዎቹ ትዉልዳቸዉን ከአፋሮች ጋር የሚያስተሳስሩ ዜጎች ብቻ ሊሆኑ ነዉ ። እንዲህ እንዲህ እያለ ሁሉም የተወለደበትን አካባቢና ጉጥ ብቻ ሲመለከት ታላቂቱ አገራችን ኢትዮጵያ ትረሳለች ። በሳቢያዉም የዘረኞችን አገር አጥፊ ደባ የምንመክትበት የህብረት ክንዳችን ይዝላል ።ቤንሻንጉል ዉስጥ በወገኖቻችን ላይ የደረሰዉን ሥቃይና እንግልት በማውገዝ ኢትዮጵያዉያን ሁሉ ከያሉበት በመዉጣት በጋራ ያሰሙት ጩኸት ለወደፊቱ የወያኔን እብሪት ለማብረድ ሊኖረን የሚገባዉን የአንድነት ቁርጠኛ አቋም በአርአያነት ያመላክታል ። ጩኸት የሚደምቀዉ ፤ትግልም ጠላትን የሚያነዝረዉ በሕብረት ሲጎሰሙበት ብቻ ነዉ።

ወያኔ በቡድንም ላይ ይሁን በግለሰብ ታጋዮች ላይ የሚያደርሰዉ ጥቃት ሁሉ ዞሮ ዞሮ ከተፈጠረበት ጸረ -ኢትዮጵያ ዓላማ ጋር የተሰናኘና በዜጎች ልቡና ዉስጥ በሚንቀለቀለዉ የኢትዮጵያዊነት እሳት ላይ ዉሃ ለመቸለስ የሚያነጣጥር ነዉ ። የአራት ኪሎዉን ቤተ መንግሥት በተቆጣጠረበት ሰሞን የኢሕአፓዉን ታጋይ-ጋይም ገ/እግዚአብሔርን ከብቦ የገደለዉ፤ ጋይም የትግራይ ተወላጅ በመሆኑ አልነበረም ። ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ በእሥራት ማቅቀዉ የሞቱበትም ሆነ አሰፋ ማሩ በአደባባይ በጥይት የተደበደበበት ምክንያት ከዘር ግንዳቸዉ እጅግ የላቀ ኢትዮጵያዊ ራዕይ የነበራቸዉ ሆነዉ መገኘታቸዉ ነበር ። ሰሞነኞቹ እንዱዓለም አራጌና እስክንድር ነጋም ወህኒ የወረዱለት ታላቁ ዓላማ ኢትዮጵያዊነት ነዉ ። ይህን መሰሉ በአገርና በሕዝብ ላይ የተነጣጠረ ደባ የሚከሽፈዉ ከአምባገነናዊዉ የጎሠኞች አገዛዝ ዉድቀት ጋር የመከራችን ዘመን ሲያከትም ፤ በደምና በዕንባ የተከተበዉ የግፍ ምዕራፍ ተዘግቶ በወያኔያዊዉ ዘረኛ ሥርዓት ፍርስራሽ ላይ አንዲት ሉአላዊ ክብሯ የታፈረ ዴሞክራሲያዊት አገር ስትገነባ ብቻ ነዉ ። ለዚህ ዓላማ ስምረት ኢትዮጵያን የሚወዱ ዜጎች ሁሉ በአንድነት ቆመዉ በጽናት መታገል ይኖርባቸዋል ።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል/
በነጻነቷ ኮርታ ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር/

## ደብዳቤዎች

ውድ የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

ያልታደለው ትውልድ በሚል ርእስ በአቶ አብዲ አብዱላሂ ስለተጻፈው መጽሐፍ ባለፈው እትማችሁ ያቀረባችሁትን አንብቢያለሁ። ይህን መጻፍ ገዝቼ ሙሉ ለሙሉ ማንበብ ስለምፈልግ እንዴት ማግኘት እንደምችል ብትጠቁሙኝ ከልብ አመሰግናለሁኝ።
ይልማ

ውድ አቶ ይልማ ። መጽሐፉ ታትሞ ለገበያ ከቀረበ ጥቂት ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ ባሁኑ ወቅት ገበያ ላይ የሚኖር አይመስለንም። ይሁን እንጅ ዋና ዋና ይዘቶችን በዚህ ጋዜጣ ላይ በተከታታይ የምናቀርበው በመሆኑ ይህ ይረዳዎታል ብለን እናስባለን። ወደፊት መጽሐፉ የሚገኝበትን አድራሻ ካወቅን ወዲያውኑ ልናሳውቅዎ ቃል እንገባለን።

የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

ውድ የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች የዛሬ ሦስት ዓመት የተጀመረው የዓባይ ግድብ በነሱ አጠራር የሕዳሴ ግድብ ሁካታ ከዶላር ማሰባሰብ ዘመቻ ሊወሩኝ ነው፣ ልንወጋቸው ነው፣ልንወራቸው ነው ወደሚለው ሁካታ እየተሸጋገረ ይመስላል። የባድሜ ሁኔታ ይደገም ይሆን? እናንተስ ምን ትላላችሁ?
ደበበ (ከሜሪላንድ)

እኛ የዚህ ጋዜጣ አዘጋጆች ከሕዝባችን ጎን በመቆም የባድሜ ሁኔታ አይደገምም እንላለን።

ሼሁ ወደዲሲ ይመጣሉ ይባላል፡ እውነት ነውን? ከመጡስ ምን ሊፈይዱ? እንደው የሳቸው ነገር ከሕዝባችን በተቃራኒ በመቆም ታሪክ ለማስመዝገብ ይጥራሉ። በዚህ አጋጣሚ በሰሜን አሜሪካ ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ ስፖርት አፍቃሪ ለስፓርተኞቻችን እንኳን ለ30ኛው ዓመት አደረሳችሁ የሚለው መልክቴን አስተላልፉልኝ።

ኃይሌ አስራት

እኛም ከሕዝብ የሚደበቅ ነገር እንደሌለ ስለምናውቅ እያደር ይገፋል እንላለን። መልክትዎንም በጋዜጣው በማተም ለወገንዎ እንዲደርስ አድርገናል።

የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

# ዜና ከተባለ

መስተዋት ከድሬ

## ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት ለአባይ ግድባችን ታረጂልን አሏት ።

አይታከቴው ወያኔ ነጋ ጠባ የፖለቲካ መድረኩን በአደናጋሪ አጀንዳዎች እያጨናነቀ ሕዝብ በዋና ዋና ግዳጆቹ ላይ እንዳያተኩር ማድረግ ላይ ተከኖበታል ቢባል ስህተት አይሆንም ። በሬ ካራጁ እንዲሉ የሚታለሉለት ደግሞ በርካታ ናቸው ። ለምን ይህ ሆነ ለሚለው ግን መልሱ አያሌ ነው ። በጥቅም የተገዛ አለ ። ንቃተ ህሊና ጎድሎት በአላፊ አግዳሚው የሚነዳ አለ ። ተቃዋሚ ነን እያሉ ግን የወያኔን ፖለቲካ በስልት በሚያራምዱት የተወናበደ አለ ። ማሞ ቂሎዎችም በርክተዋል ማለት ይቻላል ።

ወያኔ የሙስና ክስ ብሎ ዋና ዋንዎቹን ሳይነካ የመስዋእት በግ ያደረጋቸውን በተመለከተ ትኩረት ወደዚሁ ሆኖ የአማራው መመንጠርና ከየቦታው መባረር ተረስቷል ። ወያኔ በርግጥም ጮሌ! ከተከሰሱት መሃል እነ ጀኔራል ከንፈ መሠሎቹ በሙና መጨማለቃቸው የታወቀ ነው ። ከቡዎቹ ከተያዙት ጋር ሆና ሀገርን የዘረፈችው አዜብ ጎላ መሆኗን ደሞ ሀገር ያውቃል ።ሙስና ከትበለ የበረከት ሚስት ዋና መሆኗን፤ ስብሐት ነጋ ኢትዮጵያን ባረጀ ጥርሱም ቢሆን የጋጣት መሆኑን፤ ስዩም መስፍንና ቤተሰቡ ዘራፊ መሆናችውን፤ አባይ ጸሓዬ፤ አዲሱ ለገሰ፡ አባ ዱላ ፡ ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ፤ በጥቅሉ የወያኔና ተለጣፊዎች ቁንጮዎች በሙስና መጨማለቃቸው ምስጢር አይደለም ። የጋምቤላውን የቀድሞ ፕሬዚዳንት የ80 ሚሊዮን ብር ዝርፊያ በሰነድ ሊያጋልጥ የነበረው ተስፋዬ አሬሳ (የጋምቤላ የፋይናንስ ክፍል አላፊ ነበር) ከብዙ ማስፈራሪያ በኃላ በትንሳኤ ሆቴል ( አዲስ አበባ) በመርዝ ሰሞኑን ተገድሏል ። ወስላቶቹ በስልጣን ሹኩቻ ሲጠላለፉ እርስ በርስ ቢነዳደፉም ስርዓቱ ካልተገረሰሰ መፍትሔ የሚገኝ አይደለም።

የሙስናውን ጫጫታ የአባይ ድልድይ ጉዳይ ተከቶታል ። ይህ ድልድይ ከመጀመሪያውም የተጠነሰሰው የሕዝዝብ ዕይታ ሰሜን አፍሪካን ካጥለቀለቀ ሕዝባዊ አመጽ ለመቀየር መሆኑ የሚታወቅ ነው ። አባይን መገደብ የሚለው ፍላጎት በወያኔ ወይም በሟቹ ግብዝ መሪያቸው ሀ ብሎ የታሰበና የተጠነሰሰ አልነበረም ። ቢያንድ ከ አጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ ጀምሮ የታሰበ ነው ። ግን በአንድ በኩል የግብጽ አቅዋም ጋሬጣ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የገንዘብና የአቅም ጉዳይም ነበር ። ዛሬም ይህ ሀቅ ሆኖ አለ ። ጸረ ኢትዮጵያው ወያኔ ግን በባድሜ ጊዜ እንዳጭበረበረው ሀገር ወዳድ መስሎ በመቅረብ አባይ ይገደባል፤ ግብጽ የት አባቱ የሚሉ ተላላኦቹን በስሩና በዙሪያው ሊያሰልፍ ቻለ ። ዛሬም ኮልኩሏቸዋል ። ግብጽ ሊሰራ ተጀመረ የተባለውን ግድብ በአየር ለመድብደብ የምትችልበት ሁነታ አለ--ኢትዮጵያ እንደ ሀገር==ዕድሜ ለወያኔ-አቅሙ የላትም ለመከላከል ። በባዕድ ሀገር ሆነውና ከወያኔም ዙሪያ ቆመው ራጽ አይሉት ፋከራ የሚያሰሙት አላዋቂና ሀገርንም ከወያኔ ጋር ወደ ጥቃት የሚወስዱ ናቸው ። የግብጹ መሪ የራሱ የፖለቲካ ችግር አለውና አመሪካና እስራኤልንም እየከሰሰና ግድቡ ውሀ ያሳጣናል ብሎ የግብጽን ሕዝብ እያስፈራራ ድጋፍ ለማግኘት ቢጥርም አሜሪካም ሆነች እስራኤል ጦርነት ከመጣ ከኢትዮጵያ ጎን እንደማይቆሙ ለወያኔዎቹ ነግረዋቸዋል ።

እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ የወያኔ ጦር በራሳችን ላይ ጮቤ ቢረግጥም ግብጽን ለመቋቋም ሆነ ለመጋተር ፍላጎቱም አቅሙም እንደሌለው የምናውቀው ነው ፡ ለዚህም ነው ሀገርን ቆርሶ ብዚህ በዚያ የሸጠውና ያስረከበው ወያኔ አባይ ብሎ ና ለኢትዮጵያ ተቆርቋሮ ተነሳ ማለቱ ሞኝ ቢፈርዱለት አያውቅ ቢፈርዱበት አያውቅ ያሰኝብናል ።

ተቃዋሚ ሀይሎች የሚባሉት ሁሉ በስማየ ሰማያት ውስጥ እየቃገቡ መሆናቸውን መናገሩ ትልቅ ምስጢር ማውጣት አይደለም ። ሁሉም ያውቀዋል ። ስንቱ የምትሃት ጦር ተሰማራ? ስንቱ የልብወለድ ግብግብና ጦርነት ተካሂዶ ወያኔ ተጎዳ ደማ ? ሀያ አንድ አመታት የሕልም ጉዞና አጉል ተስፋ ጎድቶናል ። ስንቱ ጸረ ወያኔ ነኝ ባይ በወያኔ ኤምባሲ ደምበኛና ወሬ አቀባይ መሆኑን በዋሺንግተን፤ በርሊን፤ ሎንደን፤ ፓሪስ፤ ናይሮቢ ወዘተ አየን ታዘብን ። ከህደት በሽበሽ ነው ነውናም ራሳችንን ማታለልና ማንቀላፋት አንችልም ። ወያኔ ከሚያደርስብን ጥቃት ባሻገር ራሳችን በራሳችን እያደናገርን ወደ ውድቀት እንወስዳለን ። በ ሰሞኑ በአሜሪካ የኦጋር ኳስ ውድድርና በዓል ይካሄዳል። ልምድ ሆኖ በዚህ ጊዜ ስብሰባ የማይጠራ ስብስብና ቡድን የለም። ግማሹ በመድረክ ያለው ተናጋሪ ከታዳሚው ይበልጥበታል-- ግና ግድ የላቸውም ዋናው ስብሰባ አካሄድን ብሎ መለጫ ማውጣቱ ነው ። ከንቱ እንቅስቃሴ! በየዓመቱ ይህ ባልት ሲደገም ወያኔ ይስቃል ይሳለቃል ። ወደ ኢምንትነት የተፈነጠሩ ቡድን ተብየዎች እርስ በርስ ተገናኝተውና ቁጥራቸውን ጨምረው አለን ለማለት ከመጣር ይልቅ ሁሉም ባዶ ቤት ታቅፈው ይፋ ስብሰባ አደረግን ብለው ወሸትን መጠረቁን መርጠዋል ። ታዲያስ ይህ ሁሉ ከሰሞን ግርግርና ጫጫታ ውጪ ፋይዳ ቢስ ሆኖ ቀደም የተረጋጋጠ ሆነ ሳለ ለምንስ ይደጋገማል ?

የሚከተሉትን ትኩረት ሰጥተን እስቲ እናጢናቸው፡

- በረከት ስምኦን ኤርትራዊ ዘመዶቹን ለመጠየቅ ሰሞኑን ወደ ፍራንክፈርት (ጀርመን ) የዘለቀ ሲሆን ወደ እንግሊዝ ዘልቆ በዚያ የሚማረውን ልጁን ጠይቆ ከመመለሱ በፊት በርካታ የወያኔ የምስጢር ሰራተኞችን ለማግኘት ቀጠሮዎችን ማድረጉ ተጠቁሟል ።እ
- የባራክ አባማ አስተዳደር በቅጥረኛነት ያሰለፋቸውን ዋና ዋና ሎሌዎቹን የ ኢትዮጵያን ሁኔታ በተመለከተ በምስጢር ስብሰባ ሊያወያይ ነውም ተብሏል ።
- አረመኔውን የውስጥ ስለላ መዋቅር ሀላፊ ወልደስላሴን ተጻራሪ አለቃው ጌታቸው አሰፋ ከቦታው አባሮታል ።
- ሰማያዊ ፓርቲ የተብለው ወያኔ ወያነ ይሸታል ሲሉ ዶክተር መረራና በይነ ጴጥሮስ ተችተዋል ። የለም ተሳስታችኋል ብለው የያኔ ኢዴፓ ወይ ሞት ለፋፊዎችም ተቃውሚችዋል ።
- በርከታ ዜጋ ምነው ዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያትን የበላ ጅብ አልጮህ አለ እያለ ነው ።
- የለም፤ ተናል፤ ህልውና የለውም እየተባለ ባለው ኢሕአፓ ላይ ያውም ጸያፍ ርብርቡ መብዛቱ ምነዋ እያሰኘ መሆኑም ተጠቁሟል ።

## ምን ይሰማ ......አገር?



**"አገር በቤተሰብ ስትዘረፍ ወያኔ የት ነበር ?"**

(ጎልጉል ድረ ገጽ ጁን ፲፫ ፤ ፪፻፲፫ የዘገበበት ጠያቂ ርዕስ)

**• ቧ /...አብሮ እየዘረፈ ነዋ / ...የአገርን ዘረፋን በቤተሰብ ደረጃ ያቋደሰዉ "ራዕይ" የወያኔዎች መሆኑን መጎልጎል አቅቷችሁ ነዉ?(...በነገራችን ላይ ኢሃዴጋችሁን በወያኔ ተክተን ርዕሳችሁን አስተካክለነዋል ።)**

//

**"እነሱ ከአባቶቻቸዉ አይበልጡም ፤ እኛም ከአባቶቻችን አናንስም።"**

(ሰማያዊ ፓርቲ ፤ ሰኔ ፯ ቀን ፪፻፭ ዓ.ም የሰጠዉ መግለጫ ርዕስ)

**●የግብጻዉያኑን ግምት ለራሳቸዉ እንተዉላቸዉ ። እኛን በተመለከተ ግን ፤ከአባቶቻቸዉ በእጅጉ ያነሱ አያሌ ድዉያን /ድዉያት እንደፈሉብን ሰማያዊዎች አትዘንጉት ።**

//

**" ኢትዮጵያ የማናት?"**

(ኤደን መስፍን ፤ በኢትዮሚድያ ድረ ገጽ ጁን ፲፫ ፤ ፪፻፲፫ ያስነበበችዉ መጣጥፍ ርዕስ፤)

**●እልፍ አዕላፋቱ እኛ በአንድነት ተነስተን ካላስጣልናት በቀር ፤ አገራችን የምንላት ኢትዮጵያ ጥቂት ዘረኞችና ሆድ አደር ሎሌዎቻቸዉ በቅንጦት የሚንፈላሰሱባት ፤ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ጉድጓድ ምሰዉ የሚቀብሩባት ጓሮ ከሆነች ሃያ ሁለት ዓመታት ተቆጥረዋል**

//

**" .....እንደማንኛዉም ወጣት ፤ በወጣትነት ዕድሜያችን ራዲካል ነበርኩ ፤ ኢሕአፓ ነበርኩ ፤ ምናምን ነበርኩ ።"**

(የፓልቶኩ አባመላ -ብርሃኑ ዳምጤ ፤ ሜይ ፪፻፲፫ በኢሳቱ የሳምንቱ እንግዳ ፕሮግራም ቀርቦ ራሱን እንደገለጸዉ፤)

**●የዛሬዉ ዘመን ጅብ ቁርበት ለማስነጠፍ የማይታወቅበት አገር ድረስ ርቆ መሄዱ ቀርቷል እንዴ?/....እያ ጅቦ/ .እዚያዉ ምናምንቴህን ጠበቅ -ኢሕአፓን ለቀቅ/... ኢሳቴዎች ለመሆኑ የሚቀጥለዉ ታላቅ እንግዳችሁ ማን ይሆን ?/.."አባባ".ታምራት ገለታ ?/....ከወረዱ አይቀር እንደዚያ ነዉ ።**

ከገጽ 3 የዞረ

## ዜና ከተባለ

• የኤርትራው መሪ ሞት ወይም መወገድ የቅርብ ጊዜ ክስተት ይሆናል የሚሉ ማን ሰውየውን ሊተካው ነው በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ጀምረዋል ።

• አነ ጸጋዬ ገብረመድህን)ደብተራው) ይሰሓቅ፤ አምህ በለጠ ወዘተ በወያኔ እጅ ወድቀው ደብዛቸው ከ ጠፋ 22 አመት አለፈ።

• የሙስናው ክስ ወደ ኣዜብ ጎላ ሊያመራ ነው በማባሉ ሴትየዋ ራሷን ለመከላከል እየተወራጩች መሆኗ ተጋለጠ።

• ነጻ ጋዜጣ ነኝ የሚለው ሰንደቅ የሼከ አላሙዲ ንብረት መሆኑም ታወቀ።

• እስካሁን ውደ ግብጽ ያመራ ተቃዋሚ ድርጅት ለመኖሩ ተጨባጭ መረጃ የለም ። ሻዕቢያ ግን አነግ በኔው በኩል ይረዳ ማለቱ ይደመጣል ።

የወያኔ አገዛዝ ከባድ ቀውስ ውስጥ ገብቷል ። ሆኖም ካልተገፋ አይወድቅምና የተባባረ ክንድ ሊደቁሰው ያስፈልጋል ። ሕብረት እንዴት? ትግል እንዴት? ምላሽ ጠያቂ አቢይ ጉዳዮች ናቸው ። ክንቱ ወሬና ስብሰባን ትቶ በቁም ነገር ላይ ማ ተኩሩ የሚመረጥ ነው ። በርበሬ አይሆን ዕጣን ነገር አይሆን ሥልጣን ተብሏል። ከወሬው ቀነስ ከትግሉ ጨመር።

በሚቀጥለው ቸር ይግጠመን፤ ቸር ያሰማን ።


ድርጅትዎን በፍኖተ ህብረት የኢሕአፓ ድምፅ ያስተዋዉቁ!

ፍኖተ ህብረት የኢሕአፓ ድምፅ በየሳምንቱ ቅዳሜ ከ2 እስከ 3 PM በ730am ላይ በዲሲና አካባቢዉ የሚተላለፍ ሬዲዮ ነዉ፡፡


### ኢትዮጵያ ጋዜጣን

*በተለያዩ ድ`ረ ገጾች

ሀ. Eprp.com
ለ. Asimba.org
ሐ. Debteraw.com
ወዘተ.
*በ Face book (ethiopianewspaper)

## ምን ይሰማ...... አገር?

ከገጽ 3 የዞረ

**"አፈ-ጉባዔ አባ ዱላ ገመዳ በሙስና ክስ ምስክርነት ሰጡ ።"**

(ሪፖርተር ጋዜጣ ፤ሚያዝያ ፴ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም ያስነበበዉ ዜና )

• **የዘመኑ ቀልድ መቼም ማለቂያ የለዉም ።ከምስክርነት ይልቅ "ሙስናን እንዴት ማቀለጣጠፍ እንደሚቻል ኮርስ ቢጤ ቢሰጡ አይቀልልም? ።**

//

**"የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን አይነሳም ?"**

(መስፍን ሀ/ጊዮርጊስ በ "ኢትዮጵያ" ጋዜጣ ቁጥር ፱ ያስነበቡት መጣጥፍ ርዕስ)

●**"ተነስ/" ያሉት መልሰዉ እያስተኙት እንደምን ይነሳ ?/**

//

**"ፓትሪያርኩ ሙስናን በጋራ መቃወም እንደሚገባ አሳሰቡ ።"**

(ዘ ማለዳ ታይምስ ሜይ ፲ ቀን እንደዘገበዉ ፤)


●**ከራስ መጀመሩ አያጸድቅም አባታችን?/ ብጹዕነትዎ ሙስና የገንዘብ ቅብብልን ብቻ ሳይሆን አግባብ የሌለዉ የሥልጣን መተላለፍንም እንደሚያካትት እንደሚያዉቀዉ እምነታችን ነዉ ።**

//

**"ተቃዋሚና ምሁር ነኝ ባይ ሁሉ ራሱን የሚወድ ፤የአገር ኃላፊነትንና ግዴታን ተቀብሎ በተግባር የማይገልጽ ፈሪና ደካማ ነዉ ።**


(ቀመሩ ደሳለኝ በድረ ገጽ ያስነበቡት ጽሁፍ ርዕስ፤)

●**ምሁራን ሆይ ፤እንዲህም ትባላላችሁ ። ሁሉን በአንድ ሙቀጫ ከትቶ ወቀጣ ቢመስልም እዉነት የማያጣ ትዝብት ነዉና "ኤጭ ወዲያ" አትበሉት ።**





በሀገር ቤት በቅርቡ በገበያ ላይ ውሎ ከሕዝብ ባገኘው ተደናቂነት፣ በሽያጭ የመሪነቱን ቦታ የያዘው አዲስ የአማርኛ ልቦለድ መጽሐፍ - ሕልመኛዋ እናት - ለዲሲና ለመላው የሰሜን አሜሪካ አንባቢያንም በአባይ የገበያ አዳራሽ ውስጥ በመሸጥ ላይ ነው። የኢታለም እሸቴ ሌላው ተደናቂ የመጀመሪያ ልቦለድ መጽሐፍ "ምንዳ"ም አለን። ከነኝህ ድንቅ መጻሕፍት ለራሰዎ የሚገዙት ወይም ለወዳጅ ዘመድ የሚሰጡት ቅጂ ለማዘዝ አባይ የገበያ አዳራሽ ብቅ ይበሉ ወይም ስልክ ይደውሉልን።

# ትላንትና

## የቦረና ነጌሌዎቹ የኢሕአፓ ወጣቶች ሕዝባዊ ገድልበጨረፍታ ቅኝት

(ምንጭ መጽሀፍ ፤ "ያልታደለዉ ትዉልድ- እዉነተኛ ታሪክ፤)

(ደራሲ ፤አብዲ አብዱላሂ)

<u>ትግል ኩብለላ እና ስደት ፤ ከነጌሌ ቦረና - ሱማሌ ደርሶ መልስ</u> (ክፍል 2)

**" ነጻነት ነጻነት የምትሹ፤**
**ተዋጉለት አትሸሹ/**
**መሬት ለአራሹ ከታወጀለት፤**
**ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋምለት/"**

የ<u>ፅሀየፓፓ</u>ቱን የዓለም ላባደሮች ቀን (ሜይ ዴይ) ለማክበር አምሮ በተዘጋጀዉ የነጌሌ ቦረናዉ አደባባይ የወጣት ተማሪዎች ህብረ ዝማሬ ናኘበት። መፈክሮችም በጋለ ቁርጠኛ ስሜት ይዥጎደጎዱ ጀመር።

**"ኢሕአፓ ፓርቲያችን ነዉ/" ፤**
**"የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ/"**

ከዚሁ ጋር ፤የፓርቲዉና የሠራተኛዉ ዓለም አቀፋዊ ዓርማዎች ከፍ ተደርገዉ ተዉለበለቡ ። ወጣቱ ዕለቱን ተመርኩዞ ለላብ አደሮች ዓለም አቀፋዊ ትግል አጋርነቱን ለማብሰርና ኢሕአፓን ለሕዝቡ ለማስተዋወቅ መሰናዶ ሲያደርግ ሰንብቷል። ለዚህም በቡድን በቡድን እየሆን መዝሙሮችን ከማጥናቱም በላይ የመፈክሮችና ዓርማዎች ዝግጅቱን ሲያቀላጥፍ ቆይቷል ።የተቃዉሞ መፈክሮችንና ወቅታዊ የሕዝብ መብት ጥያቄዎችን በአደባባዩ ከሚተራመሱት የደርግ የደህንነት ኃይሎች አፈና ማዳን አስፈላጊ ነበር ። ለዚህም ሲባል በተዘጋጁት ዓርማዎችና መፈክሮች ላይ ደርግ በመገናኛ ብዙሐን አማካይነት የሚያላዝናቸዉ መፈክሮች እንዲለጠፉባቸዉ ተደርጓል ።

ፍተሻዉን በስልት አልፈን ወደ አደባባዩ ዕንብርት ዘልቀን ከገባን በኋላ የተሸፈኑት የተቃዉሞ መፈክሮችና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ዓርማዎች ተገላልጠዉ ለሕዝብ በይፋ እንዲታዩ አደረግን ።መፈክሮችና መዝሙሮች በታላቅ ወኔ መስተጋባታቸዉ ቀጠለ ። የደርጉ ሹማምንትና የጸጥታ ሠራተኞች በሕዝብ ፊት መታለላቸዉን ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸዉም ።የነበረዉ ሁኔታ በቅጽበት መልኩን ለዉጦ ቀዉጢ ሆነ።ወጣት ተማሪዎች በቆመጥ ፤ በሰደፍና በእፈሙዝ ይወገር ጀመር ። አደባባዩን አጨናንቀዉት የነበሩት ሰልፈኞችና ተመልካቾችም በሽብር ተዉጠዉ ከዱላዉ ለመዳን ባገኙት አቅጣጫ "እግሬ አዉጭኝ" አሉ ። ቀዩና አቧራማዉ የአደባባዩ ሜዳ በሺህ በሚቆጠሩ የወለቁ ጫማዎች ተሞላ ።የጸጥታ አስከባሪዎቹ ጭካኔ የተሞላ ተግባር ግን በአደባባዩ ዉስጥ ብቻ አልተገታም ።

የነጌሌ ቦረና ከተማ ጎዳናዎች፤ የልጆችና የወላጆች የጭንቅ ጩኸት በአንድ ተቀይጦ ተሰማባቸዉ ። የዚያን ዕለቱ ደም ፤ ቁስልና ስብራት ፤ እስራትን ግርፋትንና ስቃይን አስከተለ ።

የነጌሌ ወጣቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ከመሥዋዕትነት ጋር ፊት ለፊት ተዋወቁ ።ይበልጥ ቁርጠኛ ሆነዉ ትግሉን መግፋታቸዉን ተከትሎም ሕዝባዊዉ ጎራ እንደ ፍም የሚፋጅ ትንታጎችን ማፍለቅ ያዘ ።የዚያኑ ያህልም የደርግ እመቃ እየበረታ በመሄዱ የነጌሌ ከተማ ሥቃይንና ሞትን አርግዛ ታምጥ ጀመር ። እንቅስቃሴያችን እየሰነበተ፤ አደባባይ ላይ ከሚከሰት ስሜታዊና ግብታዊ ባህሪዉ ተላቅቆ የተቀናጀ ድርጅታዊ አሠራርን በመከተሉ የኢሕአፓ ርዕዮት በየህዋሱ የመወያያ ርዕስ ሊሆን በቃ ። ድርጅታዊ ርዕዮትን በማስረጹ ረገድም ሆነ በፕሮፓጋንዳዉና ቅስቀሳዉ መስከ የፓርቲዉ ልሳን "ዲሞክራሲያ" የተወጣችዉ ድርሻ ግዙፍ ነዉ ። የሕዝቡን ልብ በበሰለ አስተሳሰብ በመርታት ከትግሉ ተርታ ለማሰለፍና በወታደራዊዉ አገዛዝ ዉድቀት ማግስት እኩልነትና ነጻነት የሰፈነበትን ሥርዓት መሠረት ለመጣል ድርጅቱ ኢሕአፓ ያነጠረበት ዉብ ራዕይ ፤ ቀስ በቀስ ከወጣቱ አስተሳሰብ ጋር ሊዋሃድ በቃ ። ትግሉ በአካል እንግልት የሚያስከፍለዉ ዋጋ ከብደትም ሆነ መራር የሕይወት መሥዋዕት ከማንም የተሰወረ አልነበረም። ወታደራዊዉ አገዛዝየሕዝብን እምቢታና አመጽ በሚመለከት ከጅምር እንስቶ የተስተዋለበት ዐጼ በጉልበቱ -"ጨፍልቅ" ተፈጥሮም ግንዛቤ አልራቀዉም። ይሁን እንጂ፤ ፋሽስታዊዉን ሥርዓት ለማዉደም የሚደረገዉን ትንቅንቅ በአቸናፊነት ለማጠናቀቅ እስከተከፈለ ድረስ የሞትን ዐይን ትክ ብሎ ለማዬት የማይፈሩ እያሌ ዕንቡጥ ጅግኖች አቆጠቆጡ ቀዳሚዎቹ መፈክሮቻችን ሳይቀሩ ፤የሚጠብቀንን ትግል መራርነት ገና ከወዲሁ የሚያመላክቱ ነበሩ።

**"ፋሺዝም ይዉደም/" ...**
**"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም/"**

በመሆኑም እንቅስቃሴያችን ሁሉ የደርግ የደኅንነት አዉታር ዕለታዊ የክትትል ዒላማ ለመሆን በቃ።በተለይም ገጠር ዘልቀን ገበሬዉን በማደራጀት ሥራ ተጠምደን የነበርነዉ ወጣቶች የትኩረቱ ማዕከላዊ ነጥብ ተደረግን።በመጋቢት ወር አንድ አመሻሽ ላይ ሊጋጉላ ተብሎ ከሚጠራዉ ገበሬ ማህበር ዉስጥ ከገበሬዎች ጋር ስንሠራ አምሽተን ወደ ከተማ ስንመለስ ጓድ ሹና ገ/ማርያም በምስጢር ተልካ ወደኛ መጣች። እኔ፤ አደን አብዲና ኢብራሂም ዓሊ በጥብቅ በመፈለግ ላይ በመሆናችን እንድንሠወር አስጠነቀቀችን። ቀበሌ ዜሮ ፯ ከሚገኘዉ የአቶ ሺዴ ቤት ለአንድ ሳምንት ተደብቀን ሰነበትን። ሁኔታዎች ግጥምጥም አሉና ፤ የአካባቢያችን የኢሕአፓ አመራርም፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ትግራይ አሲምባ ላይ የጀመረዉን ወታደራዊ ስልጠና እንድንሳተፍ ሦስታችንንም መልምሎን ኖሯል ።

**ድርጅትዎን በፍኖተ ህብረት የኢሕአፓ ድምፅ ያስተዋዉቁ!**

ፍኖተ ህብረት የኢሕአፓ ድምፅ በየሳምንቱ ቅዳሜ ከ2 እስከ 3 PM በ730am ላይ በዲሲና አካባቢዉ የሚተላለፍ ሬዲዮ ነዉ: :

።በመሆኑም ለአዲሱ ተልዕኳችን ስኬት ከደቡባዊዋ የጠረፍ ከተማ ነጌሌ ወደደጋማዉ የኢትዮጵያ ክፍል በተገኘዉ ዘዴ መሄድ ነበረብን።

**አሲምባን አልሞ ኩብለላ ፤--ወደሰሜን፤** ነጌሌ ከተማችንን ተሰነባብተናት በጭነት መኪና የጅምጅም አዉራጃ ዋና ከተማ ወደ ነበረችዉ ክብረ መንግሥት አመራን ። እዚያዉ የነበሩ መምህራን ጓዶቻችን ተቀብለዉን ከመኖሪያ ቤታቸዉ ሶስት ወራት ከረምን።በወቅቱ በጓዶች መሃከል የነበረዉ የመተማመን፤ የመተሳሰብና የመረዳዳት ስሜት ከድርጅታዊ ፍቅርና ዲሲፕሊን የሰረጸና የሚያስመካ ነበርና ፈጽሞዉኑ ባይተዋርነት አልተሰማንም።ራሳችንን በድርጅታዊ ሥራ አስጠምደን፤ ጊዜያችንን ጽሁፎችን ከአማርኛ ወደ ኦሮምኛ በመተርጎምና የቅስቀሳ ንግግሮችን በካሴት ቴፖች ላይ በመቅረጽ አሳለፍነዉ።

በነበርንበት ሁኔታ የማንቀጥልበት አጋጣሚ ተፈጠረ ።ያስጠለሉን መምህራን በነበራቸዉ ፖለቲካዊ አቋም የተነሳ መንግሥታዊዉ የደኅንነት ክትትል በጋራ ሕይወታችን ላይ ጥላዉን በመጣሉ ከሚያንገብበዉ አደጋ ማምለጥ ግዴታችን ሆኖ አገኘነዉ ።የአለታ ወንዶንና የአዋሳን ከተሞች መሸጋገሪያ አድርገን ብዙም ሳንቆይባቸዉ ወደ ሻሸመኔ ዘልቀን ተጓዝን።በሻሸመኔዉ ቆይታችን ወቅት ፤በክብረ መንግሥት ሳለን እንዳደረግነዉ ሁሉ ከድርጅታችን ጓዶች ጋር በአደን አብዲ በኩል ግንኙነት ዘርግተን ሥራዎችን ከማቀላጠፍ አልቦዘንንም።

ከቤታችን ከወጣን አራት ወራት ተቆጥረዋል ።ከድርጅታችን በቀር አድራሻችንን የሚያዉቅ የለም፤ ወላጆቻችን እንኳ በሕይወት ስለመኖራችን የሚያዉቁት አልነበረም። ከነጌሌ የወጣነዉ በጥድፊያ እንደመሆኑ ከለበስነዉ ልብስ ሌላ መቀየሪያ አልያዝንም ። ጽዳት ሲያስፈልገን ያቺኑ ከነገላችን ይዘን ወደ ወንዝ ወርዶ ማጠብና እስኪትደርቅም ድረስ መለመላ ራቁታችንን ሆነን መጠበቅ ነበረብን ። በዚያን ወቅት ፤ በዉስጥ ሱሪ ብቻ ከወንዝ ዳር መለመላ ግንዱን ሲቆራመድ የነበረዉ አካላችን ዛሬም ድረስ ምስሉ በዐይነ ህሊናዬ ገዝፎ ይታየኛል። አልፎ አልፎ ፤ያን ችግራችንን ማሰላሰሌና በአሁኑ ጊዜ ከምገኝበት የኑሮ መደላድል ጋር ማነጻጸሬ አልቀረም። እስከዛሬ ድረስ ግን ፤በዚያን መሰሉ መከራ ዉስጥ ሆኜ እንኳ ፍጹም ደስተኛ የነበርኩ መሆኔን ግን ማስተባበል ከቶ አልተቻለኝም። ለሕዝብ የገባነዉ ቃል ኪዳን ጥብቀትና ለድርጅታችን ለኢሕአፓ የነበረን ፍቅር ኃያልነት ስቃይና መከራን ሳይቀር የሚያጣፍጥ ብርቱ ቅመም ነበረዉ።

ከቤተሰብ ርቀን የተጠለልንባትን ደማቋን የሻሸመኔ ከተማ ከአንድ ወር ተኩል ቆይታ በኋላ እንድንሰነባበታት ያስገደደን አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ ። በዚያች ምኔም በማትረሳኝ ዕለት እኔና ሁለቱ ጓዶቼ ሆነን ከሻሸመኔ በቅርብ ርቀት በሚገኘዉ የመልጌ ወንዶ የሥጋ ፋብሪካ ይሠራ ወደነበረ፤ መሀመድ ጃማ የሚባል የነጌሌ ልጅ ተሳፍረን ሄድን። ከርሱ ጋር ምሳ ከበላን በኋላ ወደመጣንበት መመለስ ነበረብን ። እዉነቱን ለመናገር ፤ ከርሱ ጋር በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ባደረግነዉ ዉይይት ከኛ የተለየ የፖለቲካ መስመር የሚከተል መሆኑን በማወቃችን ዘና ለማለት አልቻልንም ነበር ። የአጋጣሚ ሆኖ መኪና ላይ በመሳፈር ፊንታ በእግራችን መጓዝን መረጥን።ያ ዉሳኔያችን ከታላቅ አደጋ የሰወረን መሆኑን ያወቅነዉ በጣም ዘግይቶ ነበር ። እኛ ወደ ሻሸመኔ በመኳተን ላይ በነበርንበት በዚያ የጊዜ ፍንካች ዉስጥ፤ በጭካኔዉ አቻ ያልነበረዉና በደቡባዊዎቹ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር እንዳሻዉ የመግደል "ስልጣን" የተሰጠዉ ፋሺስቱ ዓሊ መሣ የግል ጦሩን ለአሰሳ አሰማርቶ ከተማይቱ በመበርበር ላይ ነበረች ። አጋጣሚ ሆኖ ፤ እሳቸዉ ፤ ለዐረመኔዉ ሻለቃ የደም ጥም ዕርካታ ለጭዳ የሚጣሉ ሦስት "ጸጉረ ለዉጥወጣቶችን" ከዘርዐይ ደረስ ሆቴል የመኝታ ክፍል በር ሰብረዉ ማዉጣት ሳይቻላቸዉ ቀረ ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ቃታር/ካታር-- አደገኛ ትንሽ ሀገር

ሀገሪቷ ትንሽ ናት ። የተፈጥሮ ጋዝ ካላቸው ሀገሮች ደግሞ ከሩስያና ኢራን ቀጥሎ ሶስተኛዋ ናት። የሕዝቧ ቁጥርም ምስጢር ነው ። ከሁለት መቶ ሺ አይበልጥም የሚሉ ብዙ ናቸው ። ከተቀጣሪ ሰራተኞችና "መጤዎች" ሲደመር ግን ሚሊዮን ተኩል ይሆናል ተብሎ ይገመታል ። ካታር በረሀ ላይ ያለች ትንሽ ሀገር ናት-- ሀብታም ሀገር በመሆኗና ከአሜሪካ ውጭ ያለውን ትልቁን የአሜሪካ የጦር ሰፈር የምታስተናግድ በመሆኗ በዓለም ያላት ሚዛን ዛሬ ከባድ ነው። የቃታር አደገኝነት ግን በዋና መልኩ ዋሃቢዝም/ሳላፊዝም ማለትም አክራሪ እስላምነትን ለማስፋፋት ወጥና መነሳቷና መንቀሳቀሷ ነው ። ዕድሜ ለወያኔ የሻዕቢያ ጥብቅ ወዳጅ የሆነችው ካታር በአዲስ አበባ ኤምባሲ ከፍታለች ።

ካታርን የሚመራው ኤሚር አል ትሃኒ ዝርያው ሜካን ካቃጠሉት አክራሪዎች ሲሆን አል ትሃኒ ራሱ " እኔ አዲሱ ቃራማት ነኝ" ማለቱም ይጠቀሳል ። በ ታሪክ ደግሞ ሃማዳን ቤን አሊ ቃርማት ኢብን አል አሻት የራሱን አክራሪ የሀይማኖት አንጃ ፈጥሮ በ 930 ተከታዮቹ ሜካን ማጋየታቸው ይታወቃል ። ኤሚር ሃማድ አል ትሃኒ ለስልጣን የበቃው ለውጥ ፈላጊ ነኝ ይል የነበረውን አባቱን ሼክ ካሊፋን በመፈንቅለ መንግስት ገልብጦ ነው ። ኤሚሩ በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካም የእስራኤልም ወዳጅ ሲሆን የደሞክራሲ ጠበቃ ነኝ የሚለው ከ እስቲኝ ማጭበርበር ያለፈ አልሆነለትም። ለዘመናዊ ባርነት የሚላኩትን እህቶቻችንን በማሰቃየትና ለስራ የመጡትን ሁሉ ፓስፖርት ቀምቶ በመበደልና በመበዝበዝ አረመኔ የተባለችው ካታር ከዴሞክራሲ አንጻር የፖለቲካ ድርጅቶችን ያገደች፤ ነጻ ጋዜጣ የሚባል የሌለባትና ሁሉም ውሳኔ በ ኤሚሩና ቤተሰቡ የሚወሰንባት የአምባገነን ተገዢ ሀገር ናት ።

ታዲያ ዴምክራሲን ደጋፊ ነኝ ጫጫታዋን ማን ሊያምን ይችላል? ካታር በመላ አፍሪካ ሳላፊዝምና ዋሀቢዝምን ደጋፊና የአል ቃይዳ ቡድኖች አስታጣቂና ደጋፊ ናት ። ካታር ራሷን የፈረንሳይ ወዳጅ ናት ብትልም ዛሬ በማሊ የፈረንሳይ ወታደሮች የሚታገሏቸውን አክራሪ የአልቃይዳ ደጋፊዎችን ያስታጠቀችና በግብረሰናይ እንቅስቃሴ ሽፋን የደገፈች ካታር ናት ። ካታር ዛሬ ያላትን የቢሊዮኖች ዶላር ሀብት በመጠቀም በ አውሮጳ ሀገሮች ያሉትን ተቋሞች ሁሉ እየተቆጣጠረች ናት። በበርካታ ሀገሮችም መሬት ተመርታ እርሶ አደሮችን አፈናቅላለች ። ለኢትዮጵያ ያላት እንዱ ዕቅድ ይህ ነው ። እንደ ቻይና፤ ህንድ ወዘተ ለም መሬቶችን መያዝና ሀገሬውን ማፈናቀል። ወያኔዎች ደግሞ ከፍያና ጉቦ እስካገኙ ድረስ ሌላውን ቀርቶ አደየ ትግራይ የሚሏትንም ዛሬ ባይሆን ነገ ይቸበችባሉ ።

# ነጻ ሀሳብ

ካታር የሊቢያ ወዳጅ ነበረች== ግና አሜሪካና አውሮጳ ለራሳቸው ጥቅም ብለው በጋዳፊ ላይ ሲነሱበት ካታር በሁሉም መስክ በጸረ ጋዳፊው እንቅስቃሴው ተሳትፋለች ። መሳሪያምና በመጠኑም ወታደር ልካለች ። በግብጽም በቱኒዝያም እመጽ ሳላፊስቶች የበላይነትን እንዲይዙ የተቻላትን አድርጋለች፤ አልሆን ሲላትም አክራሪ እስላማውያን የምርጫ አሸናፊ እንዲሆኑ ብዙ ሚሊዮን ለግሳለች። በምድሯ ያለው አል ጀዚራ ቴሌገርዥን ለምሳሌ የአረብኛ ክፍሉ በተለይ በአክራሪ እስላማውያን ቁጥጥር መግባቱ ምስጢር አይደለም ። በ አፍሪካ ካታር የሶማሌውን አልሸባብና የናይጀሪያውን ቦኮ ሐራም ደጋፊና አስታጣቂ ናት ። በአንድ በኩል የአልቃይዳ ቡድኖች ዋና ደጋፊ ስትሆንና ለዚህም የአፍጋኒስታን ቡድን እርዳታም በመሬቷም ቢሮ ሊጋሽ ሆና ሳለ ይህንንም ቡድን በኣይሮጵላን የሚደበድቡት ጄቶች የሚበሩት ቃታር ካለው የአሜሪካ ጦር ሰፈር የሚነሱ ናቸው ። የካታሩ መሪ ኤሚር ዋና ወዳጁ አሜሪካ ናት። አሜሪካም እሱንም ለስልጣን እየተዘጋጀ ያለውንም ልጁንም ብታስትናገድም ሌላ ይበልጥ አስተማማኝ የሆነውን ጠቅላይ ሚኒስቴር ጃሲም አል ትሃኒን ሊተኩ መፈለጋቸው ምስጢር አይደለም ። ዛሬ ካታር በአውሮጳ ብዙ ቢሊዮን ዶላር እያንቀሳቀሰች ናት ። ዋናው ተልኮዋ ደግሞ አክራሪ እስልምናን/ሳላፊዝምን ማስፋፋት መሆኑ ተተችቷል ። በአፍሪካም ካታር የምታደርገው ይህንኑ ነው ።

በየሀገሩ ሳላፊስቶችን/ዋሃቢስቶችን/ ማጠናከር ። ለም መሬትን መቆጣጠር ። ለሻዕቢያ ያን ሁሉ ድጋፍ የሰጠችውና ጅቡቲና ሻዕቢያ ሲጋጩ ዋና አስታራቂ ልትሆን ካታር የጣረችው ለኢትዮጵያ ባላት የከረረ ጥላቻ መሆኑ የተተቸና የታውቀ ነው ። ዛሬ ደግሞ ስልጡን ፖለቲካ በሚል ወያኔን እያቀፈች ኢትዮጵያን ዶጋመድ ልታደርግ እየጣረች ናት ። መሰረቷ ገንዘቧ ነው--ወያኔ ደግሞ ስግብግብ ፤ ለገንዘብ የሚገዛ ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን ነውና ሀገራችን ለአደጋ ተጋልጣለች ። ወያኔና ሻዕቢያን ለማስታረቅ ቃታር ደፋ ቀና እያለችም ናት ።

ላለፈው ዓመት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በሀይማኖታቸው ወያኔ የሚያደርገውን ህገወጥ ጣልቃ ገብነት በመቃወም አኩሪ ትግል ሲያካሂዱ ቆይተዋል-- አሁንም እየቀጠሉ ናቸው ። ይህን ትግል ለማፈንና ለማስጠላት ደግሞ ወያኔ የተቻለውን ሲጥርና የሀስትም ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት ላይ መሰማራቱን ህሊና ያለው ሁሉ ታዝቧል ። ዋናው ክሱ የሕዝብን ተቃውሞ ከነ አል ቃይዳና አክራሪዎች ጋር የሚያጣምር ነው ።

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የፍትሕ ጥያቄ ከሃይማኖቶች ጽንፈኝነት ጋር የማይያዝ ቢሆንም ዕድሜ ለወያኔ ሳላፊስቶች እንዲስፋፉ ደግሞ በሩ ተከፍቶ መቆየቱና አደጋው መኖሩ የሚካድ አይደለም ። ይህ ደግሞ እስከዛሬ የቃታር ጥረት ሳይሆን የሳውዲ አረቢያ ዋሃቢስት ስራ መሆኑም የሚደበቅ አይደለም ።

ወደ ገጽ **7** ዞሯል


## ድርጅትዎን በኢትዮጵያ ጋዜጣ ያስተዋውቁ!!!

## E mail :dc.region.eprp@gmail.com

## Tel: (202) 291 4217

### ኢትዮጵያ ጋዜጣን

*በተለያዩ ድረ ገጾች

ሀ. **Eprp.com**

ለ. **Asimba.org**

ሐ. **Debteraw.com** ወዘተ...

*በ **Face book**

ያገኙዋታል!

ትግል ኩብለላ እና ስደት ፤ ከነጌሌ ቦረና - ሱማሌ ደርሶ መልስ

ከገጽ 5 የዞረ

ለአሲምባ የታለመዉና ሻሸመኔ አድርሶን የነበረዉ ጉዟችን ወደ ደቡብ መልሶ ሳበን ።53 ኪሎሜትሮች ወደ ደቡብ ተመልሰን ይርጋ ዓለምን መጠለያችን አደረግናት።ከሦስት ወራት በላይ በጉያዋ የደበቀችን ከተማ ጎራ በለየ የትግል ገሞራ በመናጥ ላይ ነበረች ። ከአንድ ነጋዴ ቤት አረፍን ።ዉለን አድረን ፤ አሲምባ ደርሶ የትጥቅ ትግሉን ለመቀላቀል የታቀደዉ ጉዟችን በየደረስንበት ሁሉ ሰፍኖ በነበረዉ ዉጥረት ሳቢያ እየተስተጓጎለ መሄዱ ሃሳብ ላይ ጣለን። ሆደ ባሻነትም ተጠናወተን። ወቅቱ እጅግ አስፈሪ ነበርና ወደ ደጅ ወጣ ተብሎ ንጹህ አየር እንኳ በወጉ ለመማግ የሚቻልበት አልነበረም። ከጭንቀት ለመዳን ራሳችንን ባተሌ ማድረጉን መረጥን። ከአዲስ አበባ የሚላኩ በራሪ ወረቀቶችን እናባዛለን ።በአካባቢዉ የሚበተኑና የሚሰራጩ ጽሁፎችን እንገለብጣለን።መጽሐፍት ማንበብና በጽንሰ ሃሳቦች ላይ መወያየትና መከራከር ዕለታዊ ተለምዶዎቻችን ነበሩ ። አንድ ቀን እንዲህ ሆነ። የስታሊንን " የብሔር ጥያቄ" አንብበን በይዘቱ ላይ ዉይይት ከፈትን። በጽሁፉ የተሰጣቸዉ የ"እስከ መገንጠል" መብት በተግባራዊ አፈጻጸሙ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምን ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል መከራከር ጀመርን። በከርከራችን ወቅት ጓድ አደን ብዙዉን ጊዜ በስሜት የተዋጠና ኃይል የቀየጠ አቀራረብ ሲጠቀም በማስተዋላችን ተበሳጨንበት። ከጅብደኛንትና ከአምባገነናዊነት አዝማሚያ ጋር ያዛመድነዉን ምግባሩን በመኮነን በሂስ አብጠለጠልነዉ ። ጠንከር ባሉ ቃላትም ጎነጥነዉ ። በሁኔታችን የተደናገጠዉ አደን ለጥቂት ጊዜ ምንም ሳይናገር በጥያቄ አተያይ ሲያፈጥብን ቆዬ ። ከዚያም አቀርቅሮ ዕንባዉን ያዘራ ጀመር ። ፊቱንም ወደ ግድግዳዉ አዙሮ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ።ግራ የመጋባቱ ተራ ለኛ ደረሰና በዝምታ ተያየን ። ልናግባባዉ ብንሞክርም ጭርሱኑ ባሰበት። ሁላችንም ሆደ ባሻዎች ነበርንና ሳይታወቀን አብረነዉ መላቀስ ጀመርን። ያን ያህል እስኪያንሰቀስቀዉ ድረስ ሆድ ያስባሰዉንና ትንቢት አከል ምክንያቱን ትንሽ ዘግይቶ ነገረን ። "እኔ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ፤ ከእናንተ በፊት እሞታለሁ ። በትክክል ይታየኛል ።ያስለቀሰኝ ትችታችሁ ሳይሆን ከሞትኩኝ በኋላ ታሪኬን ስትመሰክሩ በዚህ መልኩ ጀብደኛና አምባገነን እንደሆንኩ አድርጋችሁ እንደምትገልጹኝ አስቤ ነዉ ያለቀስኩት ፤" በማለት ግድግዳዉን ተደግፎ ዕንባዉን አንገርቀገረቀዉ ።በድንገተኛ የሃዘን ዉርጭ ተመታን። ስለሕዝብ ፍቅር የሚፈስ የንጹህ ሰዉ ደም ታየንና እንላቀስ ጀመር። እዉነቱን ለመናገር፤ ሁላችንም በዚያ የግፍ ዘመን አሰቃቂ እንግልት ዝለን ነበር።

ይርጋዓለም ዉስጥ ከዚያን ጊዜ በላይ መቆየታችን ለደኅንነታችን አደገኛ ነበር ። ወደ አሲምባ በመሄድ የትጥቅ ትግሉን ለመቀላቀል የነበረን ዕቅድ አላስፈላጊ መስዋዕት እንዳያስከፍለን በመስጋታችን ዉሳኔያችንን ዳግም ለመከለስ ተገደድን ። በዚህም ወደ ነጌሌ ቦረና ተመልሰን በመሄድ ገጠር ገብተን ለመቆየት ወሰንን። ድርጅታችን በቀየሰልን ስልት ዘመድ እንደሞተብን ሆነን ፤ ለዚሁም በተሰናዳልን የሐዘን ልብስና የራስ ቆብ ተመሳሰለን

እኔና ኢብራሂም በቀጥታ ወደ ከብረ መንግሥት ስንጓዝ አደን ደግሞ ወደ አዋሳ አመራ ።ከከብረ መንግሥትም ነጌሌ ገባን ። ከሁለት ሳምንታት በኋላ አደንም ወደዚያዉ መጣ ። አደን ወደ ነጌሌ ሲገባ በመታየቱ እርሱን ለመያዝ የተጠናከረ አሰሳ ተጀመረ ።

ሆኖም ድርጅታችን ያወጣዉ ስልት በእርሶ አደሩ ሙሉ ትብብር ተግባራዊ ሆኖ እንደ አብዮት ጥበቃዎች ሉብሰንና ታጥቀን በምሽት ቀጠሮ በተለያዩ አቅጣጫዎች ከተማዉን ለቅቀን ወደ ገጠር ወጣን ።

በዚያኑ ሰሞን አንድ ድንገተኛ ሁኔታ ተፈጠረ ። አገዛዙ በነጌለና በአዋሳ ወህኒ ቤቶች "ወንበዴ ትቀልባለህ" በሚል አንድ ዓመት ያህል አስሮ ያንገላታዉ አቶ አሊ ኮንሶ ፤ የካቲት ፳፫ ቀን ፩፱፻፷፱ ዓ.ም በዕለተ ዓርብ ከመኖሪያ ቤቱ እንዳለ በሶማሌ አቦ ሽማቂዎች ተገደለ ። ሽማቂዎቹን ሰዎች ለመያዝ በተደረገዉ ከበባና የተኩስ ልዉዉጥ የ፺ አለቃ ሸዋ ታጠቅና የ፲ አለቃ ሞገስ የተባሉ ወታደሮች ተሠዉ ። አገዛዙ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የወንበዴዎቹን ድርጊት ከተማ ዉስጥ "ጸረ-አብዮት" የሚል ስያሜ ሰጥቶ ከሚያሳድዳቸዉ የሕዝብ ልጆች ጋር አያይዞ ከተማዉን በጦር ሠራዊት አጥሮ አሰሳዉንና ማሳደዱን አጧጧፈዉ ። በሰፈነዉ ዉጥረት ሥጋት የገባቸዉ ቤተሰቦቼ ፤ ገጠር ዉስጥ ተቀበሎ ወዳስጠጋኝ አጎቴ በላኩት ጥብቅ የአደራ መልዕክት መሠረት ከነበርኩበት እንዳልንቀሳቀስ በመደረጌ ከነአደን ጋር በያዝነዉ የቀጠሮ ቀን መገናኘት ሳልችል ቀረሁ ።

አደንና ኢብራሂም ከመርሳ ተነስተዉ ነጌሌ እንደገቡ ፤ አደን ሲያድኑት ከነበሩት ጠላቶቹ እጅ ወደቀ ።በመምህር ሙሉጌታ ዘሩ በሚታዘዝ አሳሽ ቡድን ነበር የተያዘዉ ። በይርጋ ዓለሙ ቆይታችን ወቅት እንደተነበየዉም ከሦስት ወራት በኋላ ተሠዋ። ኢብራሂምንም አሳድደዉት እንደነበረና እንዳመለጠ ሰማሁ ።እስከዛሬ ድረስ ግን ይሙት፤ ወይም በሕይወት ይኑር አላዉቅም ። የማፈቅራቸዉን ጓዶቼን ከአጠገቤ በማጣቴ የልቤ ብርታትና የዓላማ ጽናቴ ተፈተነ ። በቢታታ፤ በገናሌና በመዳ ወላቡ ከዘላኑ ሕዝብ ጋር ተመሳስዬ ለአራት ወራት ያህል ጊዜ ቆየሁ። ከተማ ዉስጥ እስራቱ ፤ ግርፋቱና ግድያ ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት በመሄዱ በፍጹም ላለመመለስ ወሰንኩ ።

ስደት -ወደ ባዕድ አገር፤

ቃታር/ካታር-- አደገኛ ትንሽ ሀገር

ከገጽ 6 የዞረ

ዛሬ ካታር በኢትዮጵያ መሬት አለሁ ስትልና እንድትፈነጭም ሲፈቀድላት በየቦታው እንዳደረገችው ሁሉ አክራሪ ሳላፊስት ቡድኖችን ለመፈልፈልና ለማጠናከር መሆኑ በጉቦ ዓይነ እውር ሆንኩ ላለውም ወያኔ ምስጢር አይደለም ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁሉም አክራሪ አል ቃይዳና ሳላፊስት ቡድኖች ከጀርባቸው ካታርን አሰልፈዋል ። እነ ቢን ላደንን ስትረዳ የነበረችው አሜሪካ ደግሞ የፖለቲካ ዕይታዋ ተንሸዋሮ የምትደግፋቸው ወይም ወዳጅ የምትላቸው ሀገሮች (ካታር፤ ሳውዲ አረቢያ ወዘተ) ዋናው ችግሮች መሆናቸውን ማየት አቅቷታል፤ወይም በጥቅም ታውራለች። ። ካታር በፍልስጤም ጉዳይ ለምሳሌ አክራሪውን ሃማስን በመደገፍ ፍልስጤሞችን መከፋፈሏ ይታወቃል ። ወደ አካባቢያችን ስንመለስ ደግሞ ካታር በቀጥታም በተዘዋዋሪም ሻዕቢያን ብቻ ሳይሆን አል ሻባብን፤ ተገንጣይ የኢጋዴንና የኦሮሞ ቡድኖችን በገንዘብ ረድታለች። ዛሬ በሶርያ ዋና አልቃይዳ የተባሉትን ቡድኖች አስታጣቂና ታዳጊ ካታር ናት ። የምዕራብና ሰሜን አፍሪካ አል ቃይዳ ቡድኖችም ዋና ረዳታቸው ካታር ናት ።

ይህች ትንሽ ሀብታም ሀገር በአለም አቀፍ ደረጃ አደጋ እየሆነች ናት ። የገንዘብ አቅሟ ትልቅ ነው ። ፍላጎቷ ደግሞ ግዙፍ ነው ። ፍላጎቷ ደግሞ አክራሪ ሳላፊዝምና ዋሃቢዝምን ማስፈን ነው ። ይህን ደግሞ መቀበል አይቻልም ። በኤኮኖሚው መስከም ካታር ሰፊ ለም መሬቶችን በቁጥጥር በማስገባት ህዝብን የምትበድል ናት-- ስለሆነም ለውድ ሀገራችን ከፍተኛ አደጋ ናት ። የቱኒዝያ ሕዝብ ካታር ከሀገራችን ትውጣ፤ ጣልቃ መግባቷ ያብቃ ብሎ የተሰለፈው በቀልድ አይደለም ። ካታር ሀገራችንን መጫወቻ ከማድረጓና ህዝባችንንም በሀይማኖት ከፋፍላ ከማናከሷ በፊት ወግጂ ውጪ ልንላት፤ ተንኮሏን ልንነቃባት ልንታገላት ይገባል ።

## ለኢትዮጵያውያን ስፓርት አፍቃሪዎች፣ ስፓርተኞችና፣ ለፌዴሬሽኑ አመራር አባላት በሙሉ የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች እንኳን ለ30ኛው ዓመት አደረሳችሁ እንላለን።

## *መርሳትን ነው መርሳት*

ከ

### ፍኖተ ህብረት ሬዲዮ የኢሕአፓ ድምፅ

*መርሳትን ነው መርሳት ተብሎ ነበር--ግን ይህ ምክር ተረስቷል ። የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ የተባለውም ወጊዎቹ አስታውሰው ቂማቸውን ሲያስተናግዱ ተወጊው በደሉን ረስቶ ደግሞ ደጋግሞ ለጠላቶቹ ሰለባ ሆኖ ሐገርንም ሕዝብንም እየጎዳ አለ ። ምነዋ ብሎ መጠየቅ ሲያንስ ነው ።*

*ሀገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ*
*የሞተልሽ ሳይሆን የገደለሽ በላ*
*ተብሏል ።*

*ባንዳና ከሀዲው፤ ነፍስ ገዳዩና ሽብርተኛው፤ ታጋይ ያስጨረሰው አንጃና ድርጅትቶችን ሊያፈርስ የተሰማራው ባንዳና በታኙ ሁኔታው አመቸኝ ብሎ የሚወራጭበት ብቻ ሳይሆን መድረኩን ሊቆጣጠር የሚጥርበት ሁኔታ ተመቻችቷል ። ለሀገር ብለው ሕይወታቸውን የሰዉት ጀግኖች ተረስተዋል ። በ አረመኔው ወያኔ እጅ ወድቀው ደብዛቸው የጠፋው የሀገር ዕንቁ ልጆች የት ደረሱ የሚልም ጥቂት ሆኗል ። በወጣት እድሜያቸው ወያኔን ብቻ ሳይሆን አጼውንም ደርግንም ሲታገሉ የባጁት ጀግኖች እነ ጸጋዬ ገብረ መድህን፤ በለተ አምሀ፤ ስጦታው ሁሴን፤ ይስሓቅ ደብረ ጽዮን ወዘተ በወያኔ እስር ቤት ታምቀው ምናልባትም ተገድለው ያለበትን ሁኔታ ብዙዎች ረስተዋል ። ግድ የላቸውም ። ዛሬ አንዳንዶች ከወያኔ እናብር ሲሉ ህሊናቸውን አፍነውና ገድለው ነው ። ማን ፕሮፌሰር አስራትን እስሮ ለሞት ዳረገ ?-- ለዚህ ተጠያቂ ሟቹ አረመኔ ብቻ ሳይሆን እነ ስዩ አብርሃምም ናቸው ። ለምን ይህ ይረሳል ? በተለይ ንስሐም ይቅር በሉንም ባልተሰማበት ? አሰፋ ማሩ፤ ተስፋዬ ታደሰ ወዘተ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል። ወንጀሉን መርሳት ምን ይባላል ? አፈወርቅ አለምሰገድ፤ ጃተኔ አሊ ወዘተ በኬንያ በወያኔ ነፍሰገዳዮች ተረሽነዋል ። ተስፋዬ ወልደ ስላሴም ወያኔንም አሜሪካንም አገልግሎ በመርፌ ተሸኝቷል--አሰየው እንበል ፤ እንርሳቸው ? የታፈኑ ጋዜጠኞች፤ የሰራተኛ ማህበር መሪዎች፤ ዜጎች ሁሉ ታፍነው የት ደረሱ ማለት ሲገባ ዝምታና ቸልታውን በምን እንተርጉመው?*

*በተለይም ወያኔን እንደግፍ ብሎ እጓጉል ጫጫታው ሲደምቅ ። የወጋ አልረሳም-- የተወጋ ግን ለምን ያንቀላፋል ? ያልደረሰብት ግልግል ያውቃልና የቆሰለውን ያልተጠቁት ቢረሱት የሚገርም አይሆንም ። በህዝብ ደረጃ ግን የደረሰበትን መከራ መርሳት አይፈቀድለትም። ትላንትን የረሳ መከራውን ይደግማል ነውና ። ዛሬ በሰበብ አስባቡ ወያኔን እንደግፍ ባዮች ትላንትን ረስተዋል ። ወያኔ በሀገርና በሕዝብ ላይ የፈጸመውን ወንጀል ዘንግተዋል ። የባሰው ደግሞ ህዝብ ፊውዳል አድሃሪ ብሎ የታገላቸውን፤ በ አጼው ዘመን ህዝብን የበዘበዙና ሕዝብ ፍዳ ያስቀበሉ ጨቋኞችን ወይም ዝርያቸውን ሀገር መልሰው ቦታ ንብረት ሲስጡ፤ በዘመነ ደርግ ወንጀል የፈጸሙትን ሲያስተናግዱ ለሕዝብና ለሀገር የታገሉትን ግን አስረው ደብዛ ሲያጠፉ፤ ሲገድሉ፤ ሲያሳድዱና ሀገር አትገቡም ሲሉ እያየን ነው ። ባለጌ ወንጀል ብንል ሲያንስ ነው ።*

*ላለው ቅንጭብ ያረግዳል ሆኖ ነው እንጂ ወያኔ ስልጣን ሲይዝም ሆነ በባድሜ ያሳየው ለማንነቱ ማወቅ በቂ በነበር ማለት ይቻላል ። የወያኔ መሪዎች ስብሃት ነጋ ተባለ መለስ ወይም ኤርትራዊው በረከት ኢትትዮጵያን አምርረው ይጠላሉ ። ሊያዋርዷት ሊያፈርሷት ይፈልጋሉ ። እየበዘበዟትም ናቸው። የመለስም የበረከት ልጆች የሚማሩት በብዙ ወጪ ቤእንግሊዝ ሀገር ነው--ሌሎችም ደግሞ ቻይና ናቸው ። ይህችን ሀገር በሁሉ መንገድ ድምጥማጧን ሊያጠፉ የተነሱ ናቸው==በመሆኑም ከነዚህ ዘረኞችና አረመኔዎች ቀና ነገርን መጠበቅ ጅልነት ነው==ሀገርን የሚጎዳ ተላላነት ። ያለፈውንም መርሳት ይቅርታ የለውም። ልጅ ሲጃጃል የ አባቱን ገዳይ ወዳጅ ብሎ ያቅፋል የተባለውን መርሳትም አያሻም ። አንዳንዶች ያወቁ የነቁ መስሏቸውና የነ ጋንዲ ሆነ ሌሎችን መርህ በቅጡ ሳይገነዘቡ በሰላማዊ ትግል ሽፋን ባርነትን እየሰበኩ ናቸው ። ይህን መስማት ከቶም አያሻም ። ወያኔ ህዝብ ጦርነት ሰልችቶታል ብሎ ሲያቅራራ እን ስዩ ደግሞ ጦርነት እንሰራባችኋለን ምርጥ ዜጎች ነን ያሉንን መርሳት አንችልም ። መርሳትን ነው መርሳት--ተጃጅሎና ተዘናግቶ ሀገርን ላለማስበላት ። ወያኔ ከግብጽና ሱዳን ሊቢያ ገጥሞ ያደረሰበንን ውርደት እንዴት እንረሳለን ? አባቴ የመናዊ ነው ኢትዮጵያውያንም አረቦች ናቸው ብሎ የለፈፈውን መለስ እንደት እንዘነገዋለን ? ነጋ ጠባ ስብሐት ነጋ ኢትዮጵያን የሚሰድበውንስ መዘንጋት ምን ይባላል ? ነጋ ጠባ ወያኔ ከድጡ ወደ ማጡ ሲወስደን ሀያ ዓመታት አለፉ-- እስከመቼስ እንዲቀጥል እንፈቅደለታለን ? መርሳትን ነው መርሳት ወገን፤*

[illegible]

*ዕርቅና ሰላም የሚሰብኩ በአብዛኛው ያልደረሰበት ግልግል ያውቃል ናቸው ። አልደመሙም፤ ወንድም እህት አልቀበሩም ። ልጆችሽን አትቅብሪም ማልቀስም ክልክል ነው የተባለች እናት የሉቻቸውም ። ስየል የደረሰባቸውም ዘመዶች የሏቸውም ። ወሬያቸው ሁሉ ባዶና ከንቱ ነው-- ስማ በለው። አስመሳይ። ነውናም በአረመኔው ወያኔ ላይ የከረረ ጥላቻ የላቸውም ። ሊያቅፉት በቋፍ ናቸው ። ወያኔ ግን ከፉ ነውና አይፈልጋቸውም ። ስገዱ ነው እንጂ ሌላ ቋንቋ የለውም ። ፊርመንልህ እንግባ ቢሉትም አሌ ብሏቸዋል ። ተጨፈኑ ላሞኛችሁ እንጂ ሌላ አቀራረብ የለውም ። የባድሜው አልበቃ ብሎ ዛሬ ደግሞ ዜጎችን አባይና ግድብ በሚል አደናግሮ ሊዘርፍና ለጦርነትም ሊማግድ የተነሳው በቂ ማስረጃ ነው ። ወያኔ ወያኔ ነውና ማንነቱን መቀየር አይችልም-- ነጋ ጠባ ግን ሰለባ ሆነው የሚታለሉለትና ሌሎችንም ሊያደናግሩ የሚጮሁት ግን ከማፈሪያ በላይ ወድዱም ጠሉም. ቅጥረኞች ሊባሉ የሚገባቸው ናቸው ። ሱሪ የሚያስፈቱ ቅማሎች ሆነዋል ::፤ ለዚህም ነው የደረስብንን መከራ ከቶምና መቸም መርሳት የሌለብን። ጋይም? ዶክተር አስራት? አሰፋ ማሩ፤ተስፋዬ ታደሰ ? ስንቱ የእስተማሪ መሪዎች? ጋዜጠኞች? በዚህ አፋችን እነ እገሌ እገሌ ይፈቱ እያልን በዚያው አፍ ደግሞ ወያኔን ደግፈን ለወያኔ ጦርነት እንሙት ድንፋታ ውጤቱ ባድሜን መድገምና ወርደትን መቀበል ነው ። ለነ በረከትና ስብሐት፤ ለነ አዜብና አዲሱ ማነው ሕይወቴን ካልሰጠሁ ብሎ የሚያቅራራ? ማነው በማያዋጣ የጦርነት ፍጥጫና ግፍጫ ገብቶ ሀገርን የሚያዋርድ፤ የሚያስጠቃ? እውን ወያኔ ለኢትዮጵያ ቢቆረቆር ከነፍሶ ገብያ ቋራ እስከ መርትራንድ ወዘተ የሀገርን መሬት ለሱዳን ይሰጥ ነበር ? ለቻይና፤ ህንድና አረቦች መሬታችንን ይቸበችብ ነበር? ስንት መቶ ሺ ዜጎችን ያፈናቅል ነበር? በየአቅጣጫው ሕዝብን ይፈጅ ይጨፈጭፍ ነበር? ይህ ሁሉ እንዴትና መቼ ተረስቶ ነው ዛሬ ወያኔ ዓባይ ግድብ እያለ ሲያደናግር አለን ከጎንህ ሊሉ የተወሰኑ ቢሆኑም ዜጎች የሚነሱት ?*

*ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል፤ መከራውን ዳግም ይቀበላል ተብሏል ። ትክክል ነው ። ሕዝብ በተለይ በገገርዎቹ አፈ ጮለኔት ከተደናገረና ጭዳ ከሆነላቸው የሀገርን ህልውና ለ አደጋ የሚሰጥ ስህተት ይሆናል ። ለወያኔ ሰለባነት የዚህን አረመኔ ቡድን ማንነት ከመርሳት የሚመነጭ ነው ። ከመርሳት። ወያኔ ማለት ጸረ ኢትዮጵያነት ነው ። ሁሉም. በየፊናው የደረሰበትን መከራና ሰቆቃ ካልዘነጋ ወያኔን ማውደም እንጂ ማቀፍ የሚለው አማራጭ የሆዳሞችና ተባባሪዎቹ ብቻ ሆኑ ይጋለጣል ። ከወያኔ ጋር ሰላምና ዕርቅን ዛሬ የሚሰብኩና የወገንና ሀገር ለቅሶን መስማት ያቃታቸው ናቸው ። ሊሞዳሞዱ የቋመጡ ከርስ አደሮች። ህዝብ ከነዚህ መራቁ ደግሞ የግድ ነው ። እንዱ አረመኔ ስለተደፋ ስርዓቱ የተለወጠ አስመስለው ማቅረብ ማደናገር ይፈልጋሉ== የሚታለሉ አጫፋሪዎች ደግሞ ተቃዋሚ ነን ከሚሉት መሀልም አሉ ። አሳፋሪ ከስተት። በቅርቡ ወያኔ ህዳሴ ግድብ ብሎ የዘረፋ፤ የማደናገሪያና የግጭት ሴራውን ሲነዛ በርታ አጆሀ ያሉለትና ለወያኔ ከወያኔ ጎን ሆነን እንሙት ያሉ (ራሳቸው ከሞት ይራቁ ቢሆኑም) ጥቂት አልነበሩም ። የኢትዮጵያ ህዝብ ህዳሴ ግድብ ብሎ ለወያኔ ግብ መሞት ሀገር ወዳድ የሚያደርገው አይደለም-- የወያኔ ሰለባ እንጂ ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀዳሚ ግዳጅ ወያኔን ከነግሳንግሱ ማውደም ብቻ ነው ። ሌላው ሁሉ መለስተኛና ቀጣይ ተልዕኮ ወይም ግዳጅ ነው ::፤ ያለው ግድብ ሁሉ ከመብራት ፈረቃ ያዳነን አይደለምና እንደ ሕዝብ አፍንጫችን ተሰንጎና በጠራራ ጸሓይ ተዘርፈን መግንባት ያለብን አጨቃጫቂ ግድብ የለም ። እንርሳ እንደናገር ካላልንስ ማነው ኢትዮጵያን ለመጉዳት በግብጽ፤ ሱዳንና ሊቢያ ተደግፎ ለስልጣን የበቃው? ማነው ለሟቹ ገዳፊ አረብ ነኝ፤ኢትዮጵያም ወደ አረብ ራቢጣ አባል ትሆናለች ያለው ? ማነው ለኢራን፤ ሱዳን፤ ወዘተ የሀይማኖት አክራሪንትን ስበኩ ብሎ በር የከፈተው? ማነው ሀገሪትዋን ለ ልዩ ልዩ ሚሲዮኖች ያጋለጠው? ማነው የሀገራችንን መሬት ትላንትም ዛሬም ለቻይና፤ለህንድ፤ ለአረቦች በገፍ እየሸጠ ያለው ? መልሱ ወያኔ የሚለው ነው ። ታዲያ ይህ ከሃዲና ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን እንዴትስ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ሊሆን ይችላል? ራሳችንን እናታልና እናወናበድ ካላልን በስተቀር ወያኔ በምንም ተዓምር ከጸረ ኢትዮጵያነቱ የሚላቀቅ አይደለም ። ለዚህም ነው ወንጀሉን መርሳት የሉብንም የምንለው ።*

*በርካታ ዜጎች ለኢትዮጵያ ሲታገሉ በወይኔ እጅ ወድቀው ጠፍተዋል ።ብዙ ሺዎች ደግሞ ዛሬም በየማጎሪያው ሰቆቃ እየተበሉ ናቸው። ብዙ ሺዎች ተሰደዋል፤ ለዘመናዊ ባርነትም ተሸጠዋል-- ህጻናትም ሳይቀሩ ። ኢትዮጵያ እየተዋረደችና እየተጠቃች ናት--በወያነ መንጋ። ይህን መርሳት ስህተት ብቻ ሳይሆን ወንጀልና ሐጢያትም ነው ።*

*የደረስብንን በደል አንርሳ* **!!**

The Ethiopian Sports Federation in North America (ESFNA) is a non-profit, tax-exempt organization founded in 1984 to promote amateur soccer and cultural events within the Ethiopian community in North America. ESFNA holds a week long soccer tournament every year. The soccer tournament as a medium, the organization's highest aim is bringing Ethiopians together for a multitude of reasons.

ESFNA's growth in North America has its roots in Ethiopians' migration to the United States and Canada—especially since the 1980s. Although there were some inter-state friendly soccer competitions in both coasts of the US amongst Ethiopians, the foundation of ESFNA was first envisioned by Ethiopians residing in the cities of Atlanta, Boston, Dallas, Houston, Los Angeles and Washington DC, , . The first tournament was held in Houston with the participation of four clubs (Washington DC, Dallas, Houston, and Atlanta) on April 20, 1984. Because of communication problem the Boston and the LA teams were unable to participate in that first tournament. A year later, the tournament was held in Washington D.C. with additional clubs.

In 1985, in addition to the soccer tournament, ESFNA member teams elected officers responsible for managing the Federation under a new format. A lot has changed since then; perhaps the most significant being the adoption of operating by-laws, tournament rules and regulation (ESFNA Disciplinary Codes) of the games and the establishment of a federal tax- exempt status in the United States.

Some of the founding principles of ESFNA were borne out of the desire for Ethiopians at the time and in the future to have something they claim as their own for generations. A week-long occasion at which Ethiopians can come together to celebrate their culture, identity and assure the continuity of their ideals in perpetuity. It was a vision of organizing a platform at which Ethiopians can come to express their humanity through sports and other cultural interactions amongst themselves and the North American community. Its goals are also providing positive role models for the youth by inviting famous Ethiopians who have done much for their country through sports, arts and the humanities.

Over the past three decades, ESFNA has become a cultural and sports Mecca for Ethiopians in North America. Every year, thousands of Ethiopians and friends of Ethiopia spend one week in one of the 25 North American cities selected as a host city; they watch dozens of soccer games amongst the 30 member clubs. Pilgrims also witness and interact with hundreds of food and dry good vendors and non-profit charitable organizations--in one venue. However, much happens surrounding the soccer tournament independent of ESFNA—which is exactly what the organization envisioned since its inception. Along the way, every year, Ethiopians spend millions of dollars in the host city--making a major contribution to the local economy.

ESFNA, by virtue of its status, has no political, religious, ethnic organization and/or other affiliations. We have adhered to this position all along because we are legally expected to take such a stance and our focus is sports and culture. However, outside of the sports events, ESFNA has contributed in initiatives to be part of development and humanitarian efforts in Ethiopia.

**Source:www.esfna.net**

## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People´s Revolutionry Party(EPRP)

ሰኔ 4 ቀን 2005 ዓ.ም.

### የወያኔ አገዛዝ ሕዝብን ለጦርነት፤ ሀገርን ለጥቃት እያዘጋጀ ነው

የወያኔ አገዛዝ የሕዝብን ትኩረት መደረግ ካለበት ወሳኝ ትግል ለመነጠል ሲያደርገው የነበረውን ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ በተመክሮ የተገነዘበው ነው። በቅርቡ ደግሞ ህዳሴ ግድብ በሚለው ማታለያ የለመደባቸውን ተላላዎች በዙሪያው እያሰለፈና ሕዝብንም እየዘረፈ ያለው አልበቃ ብሎት ግብጽን እየተነኮሰና እየቀሰቀሰ በመቀጠሉ የአባይ ውሀ አንድም ጠብታ አይቀነሰብኝም ከምትለው ከስግብግቧ ግብጽ ጋር ጦርነትን እየጋበዘ ነው።

ኢትዮጵያና ሌሎች ሀገሮች በነጭና ጥቁር አባይ የመጠቀም መብታቸው የተጠበቀ መሆኑ አያከራክርም ። በአለም አቀፍ ህግ መሰረትም ሌሎች ከወንዞቹ ተጠቃሚ ሀገሮች ውሃ እንዳያገኙ ማድረግ የሚፈቀድ አይደለም። አባይን በተመለከተ ተንኮለኛው የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሱዳንና ግብጽን ብቻ ይዞ የወሰነው የውሀ ድርሻ/ክፍፍል ትክክለኛ አለመሆኑም አከራራከሪ አይደለም--ግብጽና ሱዳን አሌ ቢሉም። ግብጽ በረሀዋን ልታለማና ሚሊዮኖችን ልታሰፍር በመፈለግ የአባይን ውሀ በተጨማሪ ደረጃ መፈለጓና የተፋሰስ ሀገሮችን ጥቅም ከቶም አላዳምጥ ማለቷም የሚደገፍ አይደለም ። ወያኔ በአሁኑ ጊዜ  ትልቅ ግድብ በሌለ ገንዘብ እሰራለሁ ብሎ የተነሳው ለኢትዮጵያ አስቦ (ወያኔና የኢትዮጵያ ጥቅም ሆድና ጀርባ ናቸውና) ሳይሆን የሕዝባዊ አመጽ ነፋስ ወደ ሀገራችንም እንዳይነፍስ በሚል የህዝብን እይታ ለማደናገር የሸረበው ተንኮል መሆኑ ክርክርን አይጠይቅም ። በኢትዮጵያ እስከዛሬ የተሰሩት ግድቦችና ገና ያላለቀው ግልገል ጊቤ ቁጥር ሶስትንም ጨምሮ ለሀገሪቷ የመብራት ሀይል ፍጆታ ከበቂ በላይ ሆነው ሳለ ዛሬም በብዙ ከተሞች መብራት በፈረቃ እየተሰጠ እንዳለ ሕዝባችን የሚያውቀው ነው። ግዙፍ ግድብ ለመገንባት መነሳትና ይህንንም ግብጽ እንደምትቃወም እየታወቀ በስልት ጉዳዩን በመያዝ ፈንታ ድንፋታና ፕሮፓጋንዳን ማስቀደሙ፤ ቦንድ ብሎ ሕዝብን ማስጨነቁና ማስገደዱ፤ ሀገር ወዳድ መስሎ ለመቅረብ መፍጨርጨሩ ሕዝብን ሊያደናግር የሚችል አይደለም። የለመዳባቸው የወያኔ የገደል ማሚቴዎችና አደናጋሪዎች --በባድሜ ጦርነት እንዳየነው ሁሉ-- ሀገር ልትጠቃ ነው ኡኡ በሚል ወያኔን በመታገል ፈንታ ሕዝብ እንዲደግፍና ከጎኑ እንዲሰለፍ ለማድረግ ከወዲሁ የተንኮል ቅስቀሳ፤ የማደራጀት ስራና ጫጫታ ጀምረዋል። ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ይህንን በሚገባ ተገንዝቦ ውጉዝ ከመ አርዮስ መባል አለባቸው።

የግብጽ ሕዝብ ጠላታችን አይደለም። አንዋር ሳዳት  የአባይ ወንዝ ከተገደበብን ጦርነት የግድ ይሆናል ያለውንም አንረሳውም--ዛሬም የግብጽ መሪ ተመሳሳይ አቅዋም በመውሰድ እሱም በበኩሉ ልክ እንደ ወያኔ ውስጣዊ ውጥረቱን ዘወር ለማድረግ ይፈልጋል። ተጨባጭ ሁኔታውንና አቅምን ሳያውቁ ሳይመዝኑ ህዳሴ ግድብ ይሰራል ብለው ጫጫታ ላይ ያሉት ክፍሎች ቅዠት ላይ ናቸው ። ከግብጽ ጋር ጦርነት ቢነሳ ይህ የኢትዮጵያ ሳይሆን የወያኔ ነው - ልክ እንደ ባድሜ። 130 ሺ ዜጋ አልቆ ምን ተገኘ? ወያኔና አጫፋሪዎቹ--አንዳንዶቹ ደግሞ ተቃዋሚ ነን ሊሉም ይጥራሉ-- ኢትዮጵያ በአባይ ልትጠቀም ስትነሳ በግብጽ ተጠቃች ወይም ልትጠቃ ነው በሚል ሀገር ወዳድ ሁሉ ተነሳ ለማለትና ለማደናገር አቅደዋል። የሚሞኙላቸው አይኖርም ማለትም አይቻልም። ለነገሩ ግብጽ ኢትዮጵያን ሊወር አይችልም-- አይሮጵላኖች አስነስቶ ግድብ ተብየውን ሊደበድብ ይችላል። የሚያቆመውም አይኖርም ። ዕድሜ ለወያኔ ስንት ሚሊዮን ብር የፈሰሰበትን አየር ሃይል በትኖ በጀሌዎቹ ሞልቶት ይቀልዳል። መካላከያ ተብየው ሆኖ ሕዝብንም ከፋፍሎና አሽመድምዶ ይገኛል ። ኢትዮጵያ መብቷን ለማስከበር አቅም የላትም። ወያኔ የአሜሪካ ሎሌና ተገዢ ነው--አሜሪካ ደግሞ ግጭት ከተነሳ ግብጽን መቃወም አንችልም/ ብላ ለወያኔ አስጠንቅቃለች። የወያኔ አገዛዝ ከድጡ ወደ ማጡ ሊከተን ነው እየጣረ ያለው። ይህን መቃወም ደግሞ ለሀገራችን  ደህንነት ወሳኝ ነውና ወያኔና ቅጥረኞቹን ወግዱ እረፉ እንበላቸው።

ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ከግብጽ ጋር ግጭቱ ለኢትዮጵያ የሚጠቅማት አይደለም። የኢትዮጵያ መንግሥት የለም ። ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ከግብጽ ጋር ተፈራርሞ የሀገርን ጥቅም መሸጡንም መርሳት አንችልም። ወያኔ ጫካ ሳለም በግብጽ መረዳቱንና የተከዜ ድልድይን ሊያፈርስ መሞከሩንም  የምንረሳው አይደለም። ወያኔ ከስረ መሰረቱ ሀገርን ለባዕድ ሻጭ ጸረ ኢትዮጵያ ሀይል ነበረ--አሁንም ነው ። ለዚህም ነው ከባዕድ ጋር የፍጥጫን ጎዳና መርጦ ሀገራችንን ለጥቃት ሊያጋልጥ እየተፍጨረጨረ ያለው። በዚህ ጸረ ኢትዮጵያዊ ጉዞው  ሀገር ወዳድ  ዜጎች ከቶም መቸም ልናጅበው አይገባም ። በባድሜ  የወደቁ ዜጎቻችን አጥንት ያወግዘናል።

በአባይ ስም አገርን ለማስጠቃት ወገንን ለማዘናጋት የታቀደውን ወያኔያዊ ሴራ በአንድነት ልናወግዝ ይገባል።


# በወያኔ እስር ቤት እየማቀቁ ያሉ ዜጎች


ሙኒር ሁሴን

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)


አንዱአለም አራጌ

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COMWEB SITE: WWW.SOCEPP.DE


በለጠ አምሃ


አበራሽ በርታ


ርዕዮት አለሙ


ጸጋዬ ገብርመድህን/ ደብተራዉ

## ሁሉም የህሊና እስረኞች ይፈቱ

ጥፋታቸዉ ምንድነዉ?



ሁሉም ይፈቱ


እስክንድር ነጋ

ከእነዚህ ሌላ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች መዳረሻቸው የጠፉ ና የተገደሉ ሲሆን ሌሎች በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ደግሞ በወያኔ እስር ቤት እየማቀቁ ይገኛሉ

## ሰዉ እንዲህ ይከፍላል


(በሕያዉ ቃል)


አንጽፍ ደብዳቤ ቢላክ አይደርሳቸዉ
እንዴት ናችሁ ብለን ፤
ከራሞት ዉሎ አዳር እንጠይቃቸዉ
ከማያዉቁት ቀዬ ርቀዉ የተጓዙ
በኃይል የተጋዙ የጠፉ ደብዛቸዉ
ከልል አድራሻዉን እግዜር ከማያዉቀዉ ፤
ለአገር ከተመኙት የነጻነት ዉሃ ተጠምተዉ ጠብታ
ለወገን ካለሟት የሙብት ደማቅ በፍታ
ተነፍገዉ ፍልቅታ
ጨረር የምትሰርግ በሽንቁር ቀዳዳ
በዘረኞች ትፋት የጭካኔ ለበቅ
ፍርሃት በሞሸረዉ የድዉያን ስላቅ
በዘመን ወርዴዎች ጎፍናኝ የታሪክ ዚቅ
ነጋ ጠባ ነድዶ በተከነ ህሊና
ዕድሜ ትግል ሥቃይ ባጣመኑት ገላ
በገረጣ ላህይ ጥዉልግ-ልግ ዛላ
ሕያዉ ሥጋ ሲነትብ በምጥ ጭንቅ መከራ
ላትጎመራ መንፈስ ነፍስያ ዘርዝራ
ከድቅድቁ ጸሊም ፤ሽሽግ የምድር ሲዖል ፤የዘረኞች ጓዳ
ሰዉ እንዲህ ይከፍላል አሳር ቆጥሮ ፍዳ
እዉነቱና ፍቅሩ ታሪከና ሀገሩ ሕዝቡ ሆኖት ዕዳ፤
ሰዉ እንዲህ ይከፍላል
ለሕዝብ በተገባ አያጥፉት ኪዳን ቃል
ከድል ኬላ ወዲህ ላይታጠፍ ከንዱ
ላያዝለዉ ድካም ላይፈታዉ መንገዱ
የዘመናት ጽልመት ነፍሮ ከአገር አምባ
ተግ-ወገግ እስከሚል
በነጻነት ጥባት ፤መብት የርችት ብርሃን ዴሞክራሲ አበባ
ትግሉ ጎዳና ላይ ለዉብ ተምኔት ዓለም
የወደቁ ጓዶች ፍሳሽ የደም ቀለም
ላስቆነጀት ዓርማ -ዕጹብ ድንቅ ዓላማ


ሰዉ እንዲህ ይከፍላል
ከእናት ከአባት ጀግኖች በወረሰዉ ባህል
ከወያኔ ደይን መካነ ኩነኔ -ፋሺስታዊ አስተኔ
ሳይረታዉ ረሃብ ጥም ሳይሰብረዉ ጭካኔ
ካገር ወስጥ ናዚራ ካገር ቤት ደናኔ ።
እንደዚህ ይከፍላል
በጎስቋል ሥጋዉ በአንዲት ስስት ነፍሱ
ሰዉ ስትፈልግ አገር
ቦታዉ ላይ ያልታጣ፤ ወንድ አንዱ ሊቅ እርሱ
ጽዋ መከራዉን ከቶ ያላሳለፈ-ለሌሎች ያልሰጠ
መስቀሉን ሲሸከም ዉስጡ ያልተናወጠ
አይለምጡት ጽናት አይቸልሱት ወኔ
አንፋሾ የጠላቱ የከፋ ቀን ጠኔ
በዋሸራ ቅኔ አፉን ጧት የፈታ
የጦር ሜዳዉ ገበዝ የሕዝብ መሪጌታ
ራስ ደጀን ነዉ ፍቅሩ እምነቱ ዋልድባ
ባለመነሳንስ ባለድርብ ካባ፤
እንዲህ ትከፍላለች
ችግር መከራን ጌጥ ትግሉን ብላዉ ቅርሷ
የኖይት ሙሽራ ያልኖረች ለራሷ
ሁሌ 'ምትለመልም የ'ዉነት ጽጌረዳ
ድካም ያላሸኘት ዕድሜ ልክ ከሜዳ
ቸርነቷ ትንታግ የደግነት ባዉዛ
ግብሯ እንደ ጣይቱ
የገዛ ብርሃኗን ለፍጥረት ለግሳ
ብርሃን የሆነችን ያገር ሕይወት ቤዛ፤
እንዲህ ይከፍላሉ
በዋሉበት ሁሉ ከቶ ያላሳፈሩ ተጋዳይ አርበኞች
ጠላት አሸባሪ ተናዳፊ ተርቦች
ወንድም የሕዝብ ልጆች
ጊዜ አይተዉ ያልከዱ በቀን ያላነሱ
'ሳት የፈተናቸዉ ቆራጦች እነርሱ፤
እንዲህ ይከፍላል ሰዉ ሰዉ ይከፍላል እንዲህ
ባገር ክብር ቅናት በሕዝብ ፍቅር እልህ
እንዲህ ይከፍላል ሰዉ፤ ሰዉ ይከፍላል እንዲህ
እንዲህህ ..................................
................/


## ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ደብዛቸዉ የጠፉ የኢሕአፓ አመራር አባላትና ነባር አባሎች


አበራሽ በርታ (መሃዛ)


በለጠ አምሃ


ጸጋዬ ገብረመድህን (ደብተራው)



ለማ ሀይሉ


ተስፋዬ ከበደ (አቦሆይ)


ይሳቅ ደ/ጽዮን


ተከይ/አሉላ


ሃጎሥ በዛብህ


ደሳለኝ አምሳሉ


ስጦታው ሐሰን


አበበ አይነኩሉ


ሞት ባይኖር



ወንዱሲራቅ ደስታ



ጋዜጠኛ ብርሃኑ እጅጉ


ኢዮብ ደስታ


ደምሴ ተስፋዬ

## በወያኔ የተገደሉ


ተስፋዬ ታደሰ


ገብረእግዚአብሔር (ጋይም)


አሰፋ ማሩ


ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ


ጀተኒ አሊ


አፈወርቅ አለምሰገድ

**ከእነዚህ ሌላ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች መዳረሻቸው የጠፉ ና የተገደሉ ሲሆን ሌሎች በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ደግሞ በወያኔ እስር ቤት እየማቀቁ ይገኛሉ**